# የወንጀል ሥነ-ሥርዓት ህግ ቅድመ ሥራ ሥልጠና

ታህሳስ 2011 ዓ.ም

ሀዋሳ፣ ኢትዮጵያ

# መግቢያ

- ወንጀል የህብረተሰቡ ማህበራዊ ችግር ሲሆን፣ ችግሩን ለመቅረፍ ወንጀል ተፈጽሞ ሲገኝ አጥፊውን በመለየት መቅጣት፣ንጹሐን ባላጠፉት እንዳይቀጡ ጥንቃቄ በማድረግ ሂደቶችን በተግባር መስራት ይጠይቃል
- የወንጀል ህግ በስራ ላይ ሲውል ሁለት ትላልቅ ጽንሰ ሀሳቦች እንዳይጠረሱ መስራት አስፈላጊ ነው 1. የህብረተሰቡን ጥቅም(ሰላም +ደህንነት) መጠበቅ 2. የዜጎች ሰብዓዊ መብት እንዳይጣስ መጠንቀቅ ናቸው። ሁለቱ ጽንሰ ሃሳቦችን በተግባር እንዳይጣረሱ ለማረጋገጥ ወንጀል ህግ ሲተገበር ህገ መንግስታዊ ሥርዓት ማበጀት፣ የሰብዓዊ መብቶችን መሰረት ያደረገ ትግበራዎችን ማድረግ አስፈላጊ ሲሆን በኢትዮጵያም በመርህ ደረጃ ህጎች ያሉ ቢሆን ተግባራዊነቱን ግን መፈተሸ ይገባል። የዚህ ስልጠና ዓላማም ህጋዊ ስርዓቱን ከተግባር ጋር በማነጻጸር መቃኘት ነው።
- የወ/ል ህግ ሥራ ላይ ሲውል ወ/ል ነው ተብሎ በህግ የተደነገገው ተፈጽሞ ሲገኝ በሥ/ሥ ህጉ መሰረት ሊፈጸሙ የሚገባቸው ተግባራት ማለትም **የፖሊስ ወንጀል ምርመራ መከናወን፣ ዐ/ህግ ክስ መመስረት፣ በፍ/ቤት ጉዳዩ እንዲታይ ማድረግ፣ ቅጣት መወሰን፣ቅጣት ማስፈጸም፣ይግባኝ መጠየቅ** ና የመሳሰሉት የሚከናወን ሲሆን የስ/ስ ህጉ የት ተጀምሮ እንደሚያልቅ በስልጠና የሚዳብር ነው

- በስልጠናው የተካተቱ 4 ክፍሎች 1. የክስ አጀማመርና የሚቋዋረጥበት መንገድ፣የወ/ል ምርመራ፣ጊዜ ቀጠሮ፣ዋስትና፣ቀዳሚ ምርመራ ና የዐ/ህግ ውሳኔ አሰጣጥ 2. በፍ/ቤት ክስ መስማት ሂደት፣የፍ/ቤት ዳኝነት ሥልጣን፣ በፍ/ቤት የቅድመ ክስ መስማት ሂደት 3. ልዩ ሥ/ሥ(ከወ/ል ሥ/ሥ ሂደት በተለየ የሚስተናገዱ ጉዳዮች 4. ይግባኝ፣ የቅጣት አፈጻጸም፣ ተከሳሽ በሌለበት የሚሰጥ ፍርድ ና ፍርዱን ቀሪ ስማድረግ
- ሥነ-ሥርዓት ህግ በራሱ በተግባር ላይ የሚያተኩር ሲሆን፣ ሰልጣኞች በጽንሰ ሃሳብ ባለፈ በተግባር ጉዳዮችን እንዲፈትሹ፣ ወደፊት በተግባር የሚያጋጥሙ ችግሮችን አውቀው የመፍሔ ሃሳብ እንዲያመነጩ ለማስቻል የተዘጋጀ ስልጠና ነው፡፡

# የወ/ል ሥ/ሥ አጀማመር፡ ፖሊስ/ባለሥልጣን /የፍትህ አካል መቅረብ/ማመልከት

- ክስ ለፖሊስ በማቅረብ/accusation: ማንም ሰው ለባለሥልጣኑ ወ/ሉን ለማሳወቅ መብት አለው
- አንዳንድ ወ/ሎች ሲፈጸም ግን ማሳወቅ ግዴታ ይሆናል
- ጉዳዩ እንዳታወቀ በፖሊስ ምርመራ ይጀመራል
- ወንጀሎቹ በህ/ቡ ውስጥ ጉዳትየሚያደርሱ(ከባድ ማህበራዊ ወንጀሎች ናቸው
- ክሱ የሚመራው በመንግስት(ዐ/ህግ) ነው
- ክስ ለማቅረብ ረጅም የይርጋ ጊዜ አላቸው
- በወ/ል ህጋችን አብዛኛው ወንጀሎች በክስ አቅራቢነት ውስጥ የሚመደቡ ናቸው
- ፖሊስ መረጃውን ካገኘ ጉዳዩን የማጣራት ግዴታ አለበት ፣ በሚስጥር ፣ በስልክ ፣በጽሁፍ፣ በኢሜይል፣በፖስታ ሊያሳውቅ ይችላል። ወንጀሉ ከፍ ያለ ማህበራዊ ቀውስ ስሊሚያስከትል ጠቁዋሚ ባይታወቅም ምርመራ ይጀመራል(ሥ/ሥ 12)

- የግል ተበዳይ ወይም ወኪሉ ማመልከት አስፈላጊ ነው( up on complaint)
- የማሳወቅ ግዴታ፣ መብት ሌላ ሰው የለውም ፤ ለማመልከት የግድ የተበዳይ ፈቃድ አስፈላጊ ነው
- ጉዳዩ መፈጸም ቢታወቅም የግል ተበዳይ ወይም ወኪሉ ፈቃድ ከሌለ ምርመራ አይጀመርም
- ግላዊ ባህሪ ያላቸው(የከፋ ማህበራዊ ጉዳት የማያደርሱ) ናቸው
- ክስ ማቅረብ፣ማንሳት፣በዕርቅ መጨረስ፣መተው የመሳሰሉት የጉዳዩ ዕጣ ፈንታ በግል ተበዳዩ ፈቃድ ላይ የተመሰረተ ነው
- በ3 ወር የክስ ማቅረቢያ(አጭር የይርጋ ጊዜ) አላቸው፣ ይህ ጊዜ ካለፈ አቤቱታ ተቀባይነት የለውም፣ ክስ ቀርቦም ቢሆን ይቆማል (ወ/ል/ህ 212፣213)
- በወንጀል ህጉ ልዩ ክፍል በግልጽ በግል አቤቱታ የሚቀርቡ ተብለው የተገለጹትን ብቻ ይመለከታል
- ተበዳዩ ራሱ ወይም ወኪሉ ቀርቦ ካላመለከተ ምርመራ አይጀመርም

# ክስ አጀማመር

- በጥቆማ መሰረት ምርመራ ከመጀመሩ በፊት ግን የሰብዓዊ መብት ጥሰት እንዳያስከትል መጠንቀቅ ያስፈልጋል / እንዳንድ ጥቆማው የተደረገው በተንኮል ሆነ በስህተት ሊሆን ስለሚችል መጠንቀቅ ያስፈልጋል/
- የምርመራ ሂደቱ/የፍርድ ሂደቱ ተራ በተራ የሚከናወን ነው፡፡ በፖሊስ ማመልከት - የምስክር ቃል መቀበል- ኤግዚቢት- ተጠርጣሪን መጥራት- የፍ/ቤት ትዕዛዝ/የብርበራ ትዕዛዝ መጠየቅ- ተጠሪን መያዝ- ዋስትና- ለፍ/ቤት ክስ ማቅረብ
- ተበዳዩ ቀርቦ በማስረጃው ካላረጋገጠ በስተቀር ሰው ስለማይያዝ ና ስላይጠራ ሰብዓዊ መብት ጥሰት የመከሰት ዕድል ጠባብ ነው
- ተመሳሳይ ነው

# እጅ ከፍንጅ ወንጀል የክስ አጀማመር

- ትርጉም፥ አድራጊው ወ/ሉ ሲፈጸም ከተያዘ፣ ለመፈጸም ሲሞክር ወይም ወ/ሉን እንደፈጸመ ወዲያውኑ ከተያዘ(19/1)
- መሰል ሁኔታዎች እንደ እጅ ከፍንጅ ይቆጠራል፥ ወ/ል አድራጊው ተግባሩን ከፈጸመ በሁዋላ ወዲያውኑ ሲሸሽ ምስክሮች ወይም ህዝብ የተከታተሉት ወይም የህዝብ ጩኸትና እሪታ የተሰማ እንደሆነ ወይም ወንጀል ተፈጸመ በተባለበት ቦታ ወዲያውኑ ፖሊስ የተጠራ እንደሆነ ወይም ወንጀሉ ሲፈጸም ወይም እንደተፈጸመ በቦታው የድረሱልኝ እሪታ የተሰማ እንደሆነ(ወንጀለኛው ወዲያውኑ ባይያዝም የእጅ ከፍንጅ ወንጀልነቱን አያስቀረውም) አንቀጽ 19(2)+20
- አቤቱታ ባይቀርብም በፖሊስ ምርመራው በቀጥታ ሊጀመር ይቻላል
- የምርመራ ሂደቱ ቀላልና ስለሚፈጥን እንዲሁም ህጉ ስለሚያስገድድ ፈጣን ፍትህ ለመስጠት አመቺ ነው( RTD,NDJ) ለምሳሌ ቁልቢ ገብርኤል ንግስ፣ ጃንሜዳ ጥምቀት በዓል የሚከናወኑ ፈጣን ፍትህ አሰጣጥ መመልከት ይቻላል

# የወንጀል ፍትህ ሂደት ስለሚቋረጥበት ሁኔታ

- የተጀመረው የምርመራና ክስ ሂደቱ ሙሉ በሙሉ በህግ አግባብ ሳይጠናቀቅ ሊቋረጥ የሚችልባቸው ሁኔታዎች አሉ
- ቀደም ሲል በ1949 ዓ.ም የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ውስጥ በግል አቤቱታ የቀረበ ክስ አቤቱታ አቅራቢው ሲያነሳው ሂደቱ በዚሁ ተቋዋርጦ እንዲቀር የሚያደርግ ድንጋጌ ነበረው። የወ/ል ህጉ ሲሻሻል በግል ተበዳይ አቤቱታ የሚቀርቡ ጉዳዮች የሚቋዋረጡበትን ሁኔታ የሚገዙት ሥ/ሥርዓት ነክ ድንጋጌዎች ሳይካተቱ ቀርቱዋል ። በዚህ ረገድ ሥ/ሥ ህጉም አልተሻሻለም
- ሌሎች የወ/ል ሥ/ሥ ሂደቱ ማቋዋጫ ምክንያቶች ወይም ሁኔታዎች ፤የተከሳሽ መሞት (ሥ/ሥ/ህ 39)፣ ለአቅመ ወንጀል አለመድረስ(39)፣ የተጠርጣሪው፤ የተለዩ፤መብቶች/ያለመከሰ/39/፣የተከሳሽ አለመገኘት/42/1፣የክስ መነሳት/122/ ወዘተ.

# ጥያቄ

- በኢፌዴሪ ወንጀል ህግ መሰረት ወንጀሎችን በግል አቤቱታ(complaint) እና በክስ አቅራቢነት(accusation) የሚመደቡ ናቸው ብሎ ለመመደብ መስፈርቱ ምንድ ነው ትላላችሁ? የሚስከትሉት ማህበራዊ ቀውስ ማነስ ወይስ በህጉ በመጠቀሱ ብቻ ነው ?
- በኢ/ፌ/ዲ/ሪ/ወ/ህ በግል አቤቱታ የሚቀርቡ ወንጀሎችን የተወሰኑትን ዘርዝሩ
- እጅ ከፍንጅ ወንጀል ጉዳይ የተያዘ ሰው ከተከሳሽ ሰብዓዊና ህገ መንግስታዊ መብቶች አንጻር እንንዴት ሊጣጣም ይገባል ትላለህ ?
- በኢትዮጵያ ህግ በግል የሚቀርቡ ክሶች በግለሰብ ፍ/ቤት በራሱ እንዲከራከር ሥ/ሥ/ህጉ የሚፈቅድ ቢሆንም በተግባር ተፈተሸዋል ወይ? ቢፈቀድ ለፍትህ አስተዳደሩ ያለው ጥቅም ምንድ ነው?
- የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ቅጽ 22 መ.ቁ.141978 ላይ የተሰጠውን የህግ ትርጉም አንብባችሁ ከተረዳችሁ በሁዋላ ውሳኔው ላይ ማህበራዊና ባህላዊ እሴቶቻችንን(መታረቅ) ለማጎልበት ሲባል ቀላልና መካከለኛ ወንጀሎች ላይ ከውሳኔው በተቃራኒ(በእርቅ መጨረስ ሊፈቀድ ይገባል ወይ?) ሃሳባችሁን አንሸራሽሩ፡፡
- ፓሊስ በርብሮ ለመያዝ በቂ ምክንያት መኖሩን ሲያረጋግጥ የብርበራ ትዕዛዝ ጥያቄ አቤቱታ/ማመልከቻ/ ለፍ/ቤት ማቅረብ ያለበት ሲሆን፣የማመልከቻው ይዘት ምን ምን ሊይዝ ይገባል ትላላችሁ፡፡
- ተጠርጣሪን በካቴና ማሰርና የማረሚያ ቤት ዩኒፎርም አስለብሶ ለፍ/ቤት(ችሎት ማቅረብ) ማቅረብ በህገ መንግስቱ የተያዙ ሰዎች መብት ጥበቃ አንጻር መርምሩና ተወያዩበት፣
- በዩኒፎርሙ ላይ "ወንጀልን በጋራ እንከላከል፣ማረሚያ ተቋዋም መማሪያ እንጂ እስር ቤት አይደለም" የሚል መርህ ቃል ያለበትን ተጠርጣሪ ለብሶ ችሎት ቢቀርብስ፣ ተጠርጣሪው ልብሱን ተገድጄ ነው የለበስኩት በማለት አናንተ በተሰየማችሁት ችሎት ፍ/ቤት አቤቱታ ቢያቀርብ ምን ዓይነት ትዕዛዝ ትሰጣላችሁ?

# የምርመራ ሥራና የተቋዋማት ሚና



- ጥቆማ፣ከ ስ፣ምስክ ር ቃል፣ተከ ሳሽ ቃል መቀበል፣
- የመሰነድ/ወ ጥ ማስረጃዎች
- መበርበር

# የምርመራ ሥራና የተቋዋማት ሚና

- የወ/ል ምርመራ ስራ በፖሊስ የሚከናወን ነው ሥ/ሥ/ 9+22(1)+ የፖሊስ ማቋዋቋዋሚያ አዋጆች ሥልጣን ይሰጣሉ። ፖሊስ ምርመራውን የሚያደርገው፣ 1. ወ/ል ተፈጽሙዋል ተብሎ ጥቆማ ሲቀርብለት፣ 2. እጅ ከፍንጅ ወንጀል ተፈጽሞ ሲገኝ፣ 3. ፖሊስ በራሱ አነሳሽነት ወንጀል ስለመፈጸሙ በቂ ምክንያት ሲያገኝ ነው።
- የወንጀል ምርመራ ሥራ(ሥ/ሥ 22-37እና 49-62) ጋር በተያያዘ የሰብአዊ መብት ጥሰት እንዳያከትሉ በትግበራ ወቅት ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል።(ተጠርጣሪ መያዝ፣ብርበራና መያዝ፣ቃል መቀበል፣ማሰር ወዘተ ከሰው ልጆች ነጻነትና መብት ላይ አላግባብ ጥሰት እንዳያስከትሉ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል)
- በምርመራ ሂደት የሚከናወኑት ተግባራት ከሥ/ሥ/ህ/ቁ 22-37እና 49-62 የሚገኙ ናቸው፡-
- **1.** የምስክር ቃል መቀበል(30) ፡ ምስክሩ ያየውን፣ የሰማወንና በስሜት ህዋሳት የተገነዘበውንና የሚያውቀውን እንዲናገር ይጠየቃል። በምክሩ ቃል ቢቻ መወሰን አላግባብ ሰዎች እንዳይነጀሉ መጠንቀቅ ያስፈልጋል።ማንም ሰው በፖሊስ ሲጠራ ቀርቦ የሚያውቀውን የመመስከር ግዴታ ያለበት ሲሆን ራሱን የሚያስወነጅል ምስክርነት እንዲሰጠ ግን አይገደድም(30/2)። ምስክሩ እንዲመሰክር መደለል ና ሃይል መጠቀም ክልክል ነው(31)። በፖሊስ የሚሰበሰበው ማስረጃ የሰው ብቻ ሳይሆን የቴክኒክ፣የሰነድ፣አሻራ ና የላብራቶሪ ወዘተ. ያካትታል ። ጉዳዩን ያስረዳሉ የተባሉት ማስረጃዎች ሁሉ ማሰባሰብ አስፈላጊ ነው።
- **2**. በርብሮ መያዝ፡ የብርበራ ዓላማ ተፈጽሙዋል ለታሰበው ወንጀል ማስረጃ ማፈላለግ ነው ፣ተበርብሮ የሚያዘው ዕቃም ሌላ ወንጀል እንዳይሰራበት ለመከላከል ነው(ለምሳሌ ጦር መሳሪያ፣ ፎርጅድ መስሪያ ማሽን)። ብርበራ የሚከናወነው ህጉን ተከትሎ እንጂ በዘፈቀደ አይደረግም፣ ህጉ ራሱ ፈቃጅና ክልካይ ሁኔታዎችን አስቀምጡዋል።ምክንያቱም የሰዎች ሰብዓዊ መብት መጠበቅ የግድ ስለሚል ነው። ብርበራ በፍ/ቤት ትዕዛዝ ና ያለ ፍ/ቤት ትዕዛዝ እንደሚደረግ በሁለት ተከፍሎ ተቀምጡዋል።

# ብርበራ.......

- **ሀ/**በፍ/ቤት ትዕዛዝ በርብሮ መያዝ(33)፡ በመርህ ደረጃ ፖሊስ ብርበራ አድርጎ ማስረጃ መያዝ ያለበት በፍ/ቤት ትዕዛዝ ነው። ፖሊስ የብርበራ ትዕዛዝ እንዲሰጠው ያመለክታል፣ፍ/ቤቱም እንደሁኔታው ሊፈቅም ወይም ሊከለክል ይችላል። በብርበራ መያዝ ለፍትህ አስፈላጊ መሆኑ፣ ለጉዳዩ ማስረጃ ለማፈላለግ መሆኑ እና ወንጀሉን ለማረጋገጥ መሆኑን ፍ/ቤት ካላመነበት ለፖሊስ አይፈቅደለትም(33/1)። 33/2/ የሚያዘው ዕቃ ዓይነት ዝርዝር፣ ዕቃው ያለበት ቦታ(ቤት ፣የቤት ቁጥር ፣ልዩ ሥፍራ )፣ የተጠርጣሪው ስም ና አድራሻ መገለጽ አለበት። ጥያቄው ጠቅላላ ሊሆን አይገባም። የብርበራ ጥያቄውም በፍ/ቤት ሲፈቀድ ከተጠየቀው ዕቃ ውጭ ሌላ መያዝ እንደማይቻል፣ የተያዘው ዕቃ ዝርዝር(ቨርባል)ስለመገኘቱ በገለልተኛ (ታዛቢ) ሰው መፈረም ፣ከተያዘው ዕቃ ውጭ ተመላሽ ማድረግ፣ ብርበራ ሲያከናውን ፖሊስ ተመጣጣኝ ሃይል ይጠቀማል፣ብርበራው በሰዓት የተገደበ ነው።ልዩ ሁኔታ(exception)፡ አ/ጅ ቁ 652/2001+883/2007 ላይ በልዩ ሁኔታ የግል ህይወት ና ሚስጥር ጥበቃ (ህ/መት አ/ጽ 26 በተቃራኒ ብርበራና ስልክ፣ደብዳቤ ጠለፋ ያለ ፍ/ቤት ትዕዛዝ ይደረጋል ይላል።
- መከራከሪያ ነጥቦች (issues) ብርበራ በህገወጥ መንገድ ተደርጎ የተገኘ ማስረጃ ውጤቱ ምንድነው? 1. ህገወጡን ተግባር ፈጻሚውን በመቅጣት ማስረጃውን መቀበል 2. ህግወጥነትን ላለማበረታት ማስረጃውን ውድቅ ማድረግ (መርዛማ ዛፍ መርዛማ ፍሬ)
- **ለ/**ያለ ፍ/ቤት ትዕዛዝ በርብሮ መያዝ(32/2) ፡ 1. ወ/ሉ እጅ ከፍንጅ ተፈጽሞ ከሆነ 2. ወ/ሉ ከ3 ዓመት በላይ የሚያሥቀጣ ሆኖ የሚያዘው ዕቃ ስለመኖሩ በቂ ጥርጣሬ በፖሊስ ሲኖርና የፍ/ቤት ትዕዛዝ እስኪወጣድረስ ቢጠበቅ ዕቃው ከቦታው ይወሰዳል ተብሎ በበቂ ም/ክት ሲታመን

# የምርመራ ሥራ

- ከተጠርጣሪ አካል የሚወሰድ ማስረጃ አሰባሰብ፡
- ሥ/ሥ/ህ/ቁ 34 ፡ ተጠርጣሪው የሐኪም ምርመራ እንዲደረግለት ፖሊስ ሊያዝ ይችላል(ውጤቱን ለማስረጃነት ለመጠቀም)ይላል፡፡ ለመመርመር ፍቃደኛ በይሆንስ፣ ለምሳሌ የደም ናሙና መመርመር የአባላዘር በሽታ እና ተመመሳይ በሽታ ማስተላለፍ ወ/ሎች ለማረጋገጥ አስፈላጊ ስለሆነ በማስገደድ ማስመርመር ይቻላል ወይ? ወ/ል ህግ 514
- በህገመንግስቱ የአካል ደህንነት መብት ተረጋግጡዋል፣አስገድገድዶ የደም ናሙና ምርመራ ማድረጉን በተመለከተ የህ/መንግስቱን ድንጋጌ ከፍትህ(ህዝብ ጥቅም) አንጻር ማነጻጸር ያስፈልጋል
- ለምሳሌ የሽብር አዋጅ 652/2001 አ/ጽ 21 ከተጠርጣሪ አካል ላይ ለማስረጃነትም ሆነ ለሌላ(መረጃ) ተግባር ናሙና(ደም፣አሻራ፣ምራቅ፣ፎቶግራፍ..ወዘተ) ሊወሰድ ይችላል፣ ተጠርጣሪው ፍቃደኛ ካልሆነ ፖሊስ ተመጣጣኝ ሃይል ሊወስድ እንደሚችል ተደንግጉዋል፡፡ ተመጣጣኝ ሃይል ምንን ያመለክታል?(ምራቅ፣ደም ለመውሰድ)...የህ/ቱ የአካል ደህንነት መብትስ?
- ተጠርጣሪ ላይ ኤች አይ ቪ ምርመራን አስገድዶ ማስደረግ ከህ/መቱ አ/ጽ 19/5/ በማስገደድ የተገኘ ማስረጃ ተቀባይነት የለውም የሚለውና በአ/ጽ 26 የግል ነጻነት ተከብሩዋል ከሚለው ጋር በማነጻጸር በማስገደድ የሚደረጉ ምርመራ ላይ ህገመንስታዊነቱን መጥናት ያስፈልጋል
- በሌሎች ሀገራት/አሜሪካ ና አውሮፓ/ አሻራና መስጠትና ፎቶ መነሳት ራስን መወንጀል ካለመገደድ ጋር አይገናኝም ብለው ይወስዳሉ
- በሃገራችንስ ህ/መቱ የደም ናሙና እና አሻራ አስገድዶ ከመውሰድ ያግዳልን?

# ተርጣሪን መያዝና ቃል መቀበል

- ተጠርጣሪን መያዝ፡ የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 26(1) ተጠርጣሪውን ለመያዝ ወ/ሉ በህጉ መሰረት የሚያስዘው መሆን አለበት ትብለ ተቀምጡዋል፡፡ይህ ማለት የማስዝ ወንጀል አለ ማለት ነው(ለምሳሌ ደንብ መተላለፍ)፡፡ ወ/ል ስለመፈጸሙ ምክንያት ካለው ፖሊስ ተጠርጣሪውን ማስቀረብ ይችላል፡፡ ተጠርጣሪውን በቁጥጥር ስር ለማዋል ፖሊስ የተለያየ መንገድ ሊከተል ይችላል፡፡ፖሊስ በ 25 መሰረት መጥሪያ ልኮ ሲቀርብ፣ መጥርያ ተልኮለትም ካልቀረበ እና እንዲሁም ገና ያልተያዘና ወንጀሉ ሊያስዘው የሚችል ከሆነ በህግ በተደነገገው መሰረት ሊይዘው ይችላል፡፡(25፣26፣28፣29)
- ፖሊስ ተጠርጣሪን በሁለት ዓይነት መንገድ ሊይዝ ይችላል

1. በፍ/ቤት ትዕዛዝ መያዝ
2. ያለ ፍ/ቤት ትዕዛዝ መያዝ

ያለ ፍ/ቤት ትዕዛዝ ለመያዝ ህጉ በሚፈቅድበት ጊዜ ሁሉ ወደ ፍ/ቤት መሄድ ሳያስፈልግበቀጥታ ፖሊስ በራሱ ተጠርጣሪውን መያዝ ይችላል፡፡ሁለቱ የአያያዝ መንገዶች የየራሳቸው የተለያየ ባህሪ ስላላቸው ለየብቻ መመልከት ያስፈልጋል፡፡

# በፍ/ቤት እና ያለ ፍ/ቤት ትዕዛዝ ተጠርጣሪን መያዝ

- በመርህ ደረጃ ሁሌም ተጠርጣሪ መያዝ ያለበት በፍ/ቤት ትዕዛዝ ነው፡፡
- የመያዣ ትዕዛዝ የሚጠየቀው ፖሊስ በራሱ ሥልጣን ማከናወን ካልቻለ፣ተጠርጣሪውን ፖሊስ ጠርቶት ለመቅረብ ፍቃደኛ ካልሆነ፣የተጠርጣሪው መቅረብ የግድ አስፈላጊ ከሆነ(54)፣በሌላ ዓይነት መንገድ ተጠርጣሪውን መያዝ ካልቻለ ፣ፍ/ቤት የመያዣ ትዕዛዝ እንዲሰጠው ያመለክታል። (54) ጥያቄውም በጽሁፍ ይቀርባል።
- ፍ/ቤቱ በአቤቱታው መሰረት የመያዣ ትዕዛዝ መፈጸሙን የሚያመላክት በቂ ምክንያት/ማስረጃ/መኖሩን ፍ/ቤቱ ሊያጣራ ይችላል።
- መያዣ ትዕዛዝ ከፍ/ቤት ማውጣት ስራ እኪሰራ ተጠርጣሪው ከአካባቢ ሊሰወር ይችላል ተብሎ ሲመት መያዣ ትዕዛዝ ጥያቄ በቴሌፎን ወይም በቴሌግራም ለፍ/ቤት ሊቀርብ ይችላል።(55) ነገር ግን ከተፈቀደ በ24 ሰዓት ውስጥ ጥያቄው በጽሁፍ ተደርጎ ለፍ/ቤት መቅረብ አለበት።
- ጥያቄው ላመንኛውም ፍ/ቤት በዬትኛውም ጊዜ ሊቀርብ ይችላል።(25፤ 26፣53)። የጥያቄው ይዘትምን ዓይነት ነው፣ ጥያቄው ውድቅ ቢደረግ ፖሊስ ይግባኝ ማለት መብት አለው ወይ ?
- በበርካታ በተፈቀዱ ልዩ ሁኔታዎች ሲጋጥሙ የፍ/ቤት የመያዣ ትዕዛዝ ሳያስፈልግ ፖሊስ ተጠርጣሪን መያዝ ይችላል።እነኝህም ሁኔታዎች በህጉ በጠቅላላው ተቀምጡዋል፣ ሁኔታውም ተሙዋልቶ ሲገኝ ፖሊስ ያለ ፍ/ቤት ትዕዛዝ ተጠርጣሪን መያዝ ሥልጣን ተሰጥቶታል።
- ሁኔታዎቹም ፥ ማንኛውም ሰው ወየም የፖሊስ ሰራዊት ከ3 ወር በላይ ቀላል እስራት የሚያስቀጣ ወንጀል እጅ ከፍንጅ እየተፈጸመ ወይም ፈጽሞ ተጠርጣሪውን ያገኘው እንደሆነ መያዝ ይችላል(ማንም ሰው ግን ይዞ ለፖሊስ ያስክባል) 50
- 51(1) ሀ-ሸ ድረስ ያሉት ሁኔታዎችም ሲሙዋሉ ፖሊስ ያለ ፍ/ቤት ትዕዛዝ ተጠርጣሪን እንዲይዝ ስልጣን ተሰጥቶታል ።

# የተጠርጣሪን ቃል መቀበል (27)

- ተጠርጣሪው በፖሊስ ቁጥጥር ስር ከዋለ በሁዋላ የተያዘበት ጉዳይ ተገልጾለት/አቤቱታ ወይም ክስ/ ተነግሮት ቃሉን እንዲሰጥ ይጠየቃል።ተጠርጣሪው ቃሉን እንዲሰጥ አይገደድም። ፈቅዶ የሚሰጥ ከሆነ ግን የሚሰጠው ማንኛውም ቃል በማስረጃነት ተመዝግቦ ወደ ፊት በፍ/ቤት በማስረጃነት ሊቀርብበት እንደሚችል ሊነገረው ይገባል/Miranda Warning/right/:: በማስገደድ የተገኘ የዕምነት ቃል/ማስረጃ/ተቀባይነት የለውም/ህ/መት አ/ጽ 19(5)።
- Miranda Warning/right( Miranda vs. Arizona State):

1. ያለመናገር መብት/ዝም ማለት መብት/
2. በራሱ ላይ ምስክር ሆኖ ራስን ያለመወንጀል መብት
3. በህግ አማካሪ የመደገፍ መብት/በመቅጠር ወይም ነጻ የመ/ት ድጋፍ/
4. የቀረበበትን ክስ ወይም አቤቱታ በሚገባው ቁዋንቁዋ እንዲረዳው ማድረግ

ይህ መብት ተጠርጣሪው በቁጥጥር ሥር ከዋለበት ጊዜ ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል።

- በኢ/ያ ህግ ማዕቀፍ Miranda Warning/right ዕውቅና አለው ወይ? በኢፌዲሪ ህ/መት አ/ጽ 19(2) ላይ “ተጠርጣሪው በህግ ከለላ ከዋለበት ሰዓት ጀምሮ ያለመናገር መብት አለው” ይላል። ይህ መብቱም በሚገባው ቁዋንቁዋ ሊነገረው ይገባል። አ/ጽ 20(3) ላይ ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ እራሱን ያለመወንጀል መብት ጋር የሚገናኝ ነው።በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.27(2) ተጠርጣሪው ቃሉን ሲሰጥ ያለመናገር መብት እንዳለው ይነገረዋል ተብሎ የተደነገገ ቢሆንም ህ/መቱ ግን በቁጥጥር ሥር ከዋለበት ሰዓት ጀምሮ ሊነገረው እንደሚገባ ነው።
- 27(2) መሰረት የተሠጠን ቃል በ35 ፍ/ቤት አቅርቦ ማጸደቅ ምን ያህል በነጻነት አምኑዋል ማለት ይቻላል?
- በ27 መሰረት የተዘጋጀ ፖሊስ ጣቢያ ፎርም ላይ መብቱ የተኘገረው እንደሆነ ይገልጻል፣ነገር ግን ታዛቢ/ህግ/ባለሙያ አብሮት ሳይኖር በምን ይታመናል? መፍትሄ፡ ካሜራ/መቅረጽ/ ማዘጋጀት፣ተጠርጣሪው በህግ ቁጥጥር ስር እንደዋለ በህግ ባለሙያ እንዲታገዝ ማድረግ.ወዘተ።

# የጊዜ ቀጠሮ ጥያቄ አቀራረብ እና ውሳኔ አሰጣጥ

- በመያዣም ሆነ ያለመያዣ ትዕዛዝ የተያዘ ተጠርጣሪ ለፍ/ቤት በ48 ሰዓት ውስጥ መቅረብ አለበት(ሥ/ሥ 29+59(1) ህ/መት አ/ጽ 19/3/።ፖሊስ ተጠርጣሪውን በዋስ ያልለቀቀው ከሆነ ለፍ/ቤት ያቀርበዋል። ፍ/ቤት ከቀረበ በሁዋላ ሁለት ነገር አለ በዋስ መልቀቅ ወይም ፖሊስ ምርመራውን ያላጠናቀቀ ከሆነ ተጨማሪ የምርመራ ጊዜ በመፍቀድ ተጠርጣሪውን ማረፊያ ቤት እንዲቆይ ማዘዝ(59)።
- የጊዜ ቀጠሮ ፖሊስ ለምርመራ የሚሆነውን እና ጊዜው ለምን እንደሚያስፈልገው ከመግለጽ በተጨማሪ እንዲፈቀድለት ለፍ/ቤት ያመለክታል፤ ለምን ግዜውን እንደፈለገ፣ የጊዜው ጥያቄ አላማ፣መገለጽ አለበት።
- ፖሊስ ከፍ/ቤት ፈቃድ ለማግኘት የሚያቀርበውን ጥያቄ ምን ማስረዳት ይጠበቅበታል፣ፍ/ቤቱስ የሚፈቅደው ምን ሁኔታዎች መሙዋላቱን ሲያረጋግጥ ነው፣የጊዜ አስፈላጊነቱ በምን መስፈርት ይመረመራል(ከጉዳዩ ውስብስበነት፣ዓይነት፣ከፖሊስ ጥረት፣የማስረጃው ብዛት፣ማስረጃውን ለመሰብሰብ የግድ መታሰር ያለበት መሆኑን፣ወዘተ)?
- ፍ/ቤት የፖሊስን ጥያቄ ሊቀበለውና ከ14 ቀን ያልበለጠ የምርመራ ጊዜ ሊፈቅድና ጥያቄውን ውድቅ ሊያደርግ ና በዋስ ሊፈታው ይችላል(59/1) ፣በክርክሩ ላይ የተጠርጣሪውም ሃሳብ ሊሰማ ይገባል።መደበኛ ክርክር ይደረጋል፣በትዕዛዙ ላይም ይግባኝ ሊባልበት ይችላል።

## የጊዜ ቀጠሮ ጥያቄ አቀራረብ እና ውሳኔ አሰጣጥ

- እያንዳንዱ ዙር ጊዜ ቀጠሮ 14 ቀን አይበልጥም የሚለው ለስንት ዙር ይፈቀዳል.ገደብ አለው ወይስ የለውም? ለምሳሌ አዋጅ ቁጥር 909/ አንቀጽ 20/2/ 4 ወር የማይበልጥ ጊዜ ቀጠሮ ይሰጣል
- 14 ቀን የስራ ብቻ ወይስ በዓላትንና ለፍት ቀን ይጨምራል?
- የጊዜ ቀጠሮ ጥያቄና ፈቃድ ከህ/መቱ አ/ጽ 19/4/ና 20/1/ አንጻር እንዴት ሊጣጣም ይገባል?
- Issue: ዋስትና በሚያስነፍግ ወንጀል(ሙስና፣ነፍስ ግድያ፣ወዘተ) የተጠረጠረ ግለሰብ ላይ ፓሊስ የጠየቀው ጊዜ ቀጠሮ አልቆ ምርመራ መዝገቡን ለዐ/ህግ አስተላልፊያለሁ በማለቱ የጊዜ ቀጠሮውን መዝገብ ፍ/ቤቱ ዘጋው።ዐ/ህግ ክስ ሳያቀርብ ቢዘገይ መፍትሄው ምንድ ነው፣ የጊዜ ቀጠሮ መዝገብ ሊዘጋ ይገባል ወይ፣እስከ ዐ/ህግ ክስ ድረስ መጠበቅ አለበት ወይ?(ሰብዓዊ መብት ጥሰት ቁጥጥር አንጻር)

ፍ/ቤት ስለመቅረብ እና በዋስ ስለመልቀቅ

- በዋስትና የመለቀቅ መብት አለማቀፍ ሰብዓዊ መብት ሰነዶችና በኢፌዲሪ ህ/መት ድንጋጌዎች የተደገፈ ነው፡፡ ህ/መት አ/ጽ 17(2) ላይ ማንም ሰው በህግ ከተደነገገው ሥርዓት ውጭ ሊያዝ፣ክስ ሳይቀርብበት ወይም ሳይፈረድበት ሊታሰር እንደማይቻል ይደነግጋል፡፡ ተይዞም ከሆነ በዋስ ሊፈታ መብት አለው፡፡
- ህ/መት አ/ጽ 19(6) "**የተያዙ ሰዎች በዋስ የመፈታት መብት አላቸው፣ ሆኖም በህግ በተደነገገው ልዩ ሁኔታዎች ፍ/ቤት ዋስትና ላለመቀበል ወይም በገደብ መፍታትን ጨምሮ በቂ ዋስትና ማረጋገጫ እንዲያቀርቡ ለማዘዝ ይችላል**" .......በዚህ ድንጋጌ መሰረት በዋስ የመፈታት መብት በመርህ ደረጃ የማንኛውም የተያዘ ሰው መብት ሲሆን፣ በልዩ ሁኔታ(ምክንያት) ሊከለከል ስለሚቻል የዋስትና መብት በራሱ ፍጹም መብት ሳይሆን በህግ አግባብ ሊሸረፍ የሚችል ነው(absolute right vs. limitations/derogation)

ፍ/ቤት ስለመቅረብ እና በዋስ ስለመልቀቅ

- **ፍ/ቤት ከመቅረብ በፊት በዋስ ሰለመልቀቅ(የፖሊስ ጣቢያ ዋስ)፡** ፖሊስ የያዘውን ተጠርጣሪ በዋስ ሊለቅ ይችላል፤ ፖሊስ ሊለቅበት የሚችለው ሁኔታዎች በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 28 ላይ ተቀምጡዋል፡፡ ሁኔታዎቹም ፡ 1/ ወንጀሉ በጽኑ እስራት የማያስቀጣ መሆን 2/ ወንጀሉ ስለመፈጸሙ አጠራጣሪ ሁኔታ መኖር  ናቸው፡፡ በፖሊስ ጣቢያ በዋስ መልቀቅ በጥቃቅን/ቀላል/ ወንጀሎች ላይ ሊበረታታ የሚገባ ቢሆንም ከባድ ወንጀሎች ላይ ግን ፖሊስ ህጉን በመከተል(28) ጥንቃቄ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ህ/መት አ/ጽ 19/4/ የአካል ደህንነት፤ አ/ጽ 19/6/ የተያዙ ሰዎች በዋስ የመለቀቅ መብት እንዳለ በህጉ ተደንግጉዋል፡፡ ፖሊስ በወ/ል ጠርጥሮ የያዘውን ሰው በ48 ሰዓት ውስጥ ለፍ/ቤት የማቅረብ ግዴታ አለበት፤ ፍ/ቤቱም ተጠርጣሪው ሲቀርብ ዋስትና ሊፈቅድለት/ሊለቀው/ይችላል፡፡ (59/1/)፡፡

ፍ/ቤት ስለመቅረብ እና በዋስ ስለመልቀቅ

- የዋስትና መብት እንዲጠበቅ ወይም የአካል ደህንነት እንዲጠበቅ ለፍ/ቤት የሚቀርብ ጥያቄ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 64 +19/4/+19/6/ መሰረት ይቀርባል። በጥያቄው ላይ ፍ/ቤት የሚሰጠው ውሳኔ/ትዕዛዝ/፡-

1. በዋስትና እንዲለቀቅ መፍቀድ ፡ የጠረጠረበት ወንጀል ዋስትና የማያስነፍግ ሆኖ ሲገኝ (63)
2. ዋስትና በመንፈግ ተጠርጣሪው ማረፊያ/ማረሚያ ቤት እንዲቆይ ማዘዝ

Objective standard (የመከልከያ ምክንያቶች):- የሥ/ሥ/ህ/ቁ 63 ሁኔታ ተሙዋልቶ ሲገኝ ፡ ሀ/ ሞት +15 ዓመት በላይ ለ/ በልዩ ህጎች የተደነገጉ ወንጀሎች ዋስትና የሚያስከለክሉ ናቸው ተብሎ ዘርዝሮ ሲያስቀምጥ (ለምሳሌ በአደገኛ ቦዘኔነት ወንጀል ተጠርጥሮ የተያዘ ሰው በዋስትና አይለቀቅም፤ በሙስና ወንጀል ተጠርጥሮ/የተከሰሰ ሰው የተጠረጠረበት ወንጀል ከ10 ዓመት በላይ እስራት የሚያስቀጣ ሆኖ ሲገኝ በዋስትና ሊለቀቅ አይቻልም(883/07 አ/ጽ 4)

Subjective standard(በሁኔታ ዋስትና መንፈጊያ /መከልከል ምክንያቶች)፡ የሥ/ሥ/ህ/ቁ 67(ሀ-ሐ) ፡ ሀ/ በዋስ ቢለቀቅ ግዴታውን አይፈጽምም ተብሎ ሲገመት፤ ለ/ ሌላ ወ/ል ይፈጸም ይሆናል ተብሎ የሚገመት ሲሆን፣ ሐ/ ማስረጃ ሊያጠፋ ይችላል ተብሎ ሲታሰብ ነው። ሁኔታዎቹ (ሲገመት፣ሲታሰብ ተብሎ) ለዳኛው ግምትና ህሊና የተተወ በመሆኑ በጥንቃቄ ሊመረመር፣እንዲሁም በዘፈቀደ ባለመተው ዋስትና መብት መንፈግ ላይ ትኩረት በማድረግ በአግባቡ ሊመረመር ይገባል።(የሰበር ውሳኔዎች ይታይ 67)

ፍ/ቤት ስለመቅረብ እና በዋስ ስለመልቀቅ

- የዋስትና መብት ሲፈቀድ የዋሱን ግዴታ ያሳውቃል ፣ፍ/ቤቱ የዋስትናውን ዓይነት፣የዋስትና መጠን(የገንዘብ መጠን)፣ የዋስትናው ጊዜ ቆይታ ይወስናል ሥ/ሥ/ቁ 69+71 ። የሚወሰነው የዋስትና ግዴታ ና መጠን ከወ/ሉ ከባድነት፣ተጠርጣሪውን የሚያስገድደው መሆኑን፣የተከሳሹንና የዋሱን የሀብት መጠን፣በዋስ ሲለቀቅ ለህዝብ ጸጥታ ያለው ን አደጋ ማገናዘብ ያስፈልጋል።
- የዋስትና ግዴታ አለማክበር ዋሱ ላይ የሚስከትለው ውጤት ምንድነው? ሥ/ሥ/ህ/ቁ 76+79፡ ገቢ የማያረግበትን ምክንያት እንዲገልጽ በማድረግ ተከሳሹ እንዲታሰር ይደረጋል። ምክንያቱ በቂ ካልሆነ ገንዘቡ ይወረሳል/ገቢ ይደረጋል።
- በዋስትና ላይ የሚሰጥ ብይን/ትዕዛዝ በመደበኛው ክርክር ይመራል፣የግራ ቀኝ ሃሳብና ክርክር ይሰማል፣ይግባኝም ይጠየቅበታል(75..በ20 ቀን ውስጥ ይጠየቃል ) ይግባኝ ዐ/ህግ መጠየቅ ይችላል ወይ(ሰበር ውሳኔ ይታይ)፤ በሙስና ወ/ል ፣ሽብርር ወ/ል
- ዋስትና መብት ሊነሳ የሚችልበት ምክንያት በ 74 ላይ ተቀምጡዋል፡ ዋስትናው በማጭበርበር፣ማታለል የተገኘ ሲሆን፣ በዋስ ከወጣ በሁዋላ አዲስ ነገር (ወ/ል ከፈጸመ) ከተገኘ ወዘተ ናቸው።

# የዐ/ህግ ውሳኔ አሰጣጥ እና የፍ/ቤት ሚና

1. በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 36 ና 37 መሰረት ከፖሊስ ተጠናቆ ምርመራ መዝገብ ሪፖርት ለዐ/ህግ ይልካል፤ሪፖርቱም ምን ኣይነት ይዘትና ዝርዝር እንደሚይዝ በ36ና 37 ላይ ተገልጹዋል።
2. ከፖሊስ ተጠናቆ የቀረበ ምርመራ መዝገብ ሪፖርት ዐ/ህግ የሚሰጣቸው ውሳኔዎች/ተግባራት፥-

I. በ15 ቀን ውስጥ ክስ አዘጋጅቶ ለሚመለከተው ፍ/ቤት ክስ ያቀርባል /38/ሀ/+109/። ይህ 15 ቀን ክስ ለማቅረብ በቂ ጊዜ ነው ወይ? ጊዜው ካልበቃውና በ15 ቀን ውስጥ ክስ ካላቀረበ ውጤቱ ምንድ ነው?

II. ቀዳሚ ምርመራ እንዲደረግ ፍ/ቤትን መጠየቅ(38/ለ/+80)፥ የቀዳሚ ምርመራ ዓላማ /ጥቅም/ 80+85+84+88+89+92+144፣ በቀዳሚ ምርመራ ላይ የዐ/ህግና የፍ/ቤት ሚና፣ቀዳሚ ምርመራ በሁሉም ወንጀሎች ላይ አይረግም በ539 ና 671 ላይ ነው የሚደረገው(80/1/፣ቀዳሚ ምርመራ በወረዳ ፍ/ቤት ነው ሚታየው(81)፣ ሂደቱ (ክርክሩ/ምን ይመስላል…

III. ተጨማሪ ምርመራ እንዲደረግ ለፖሊስ ማዘዝ(38/ሐ/፥ ምልልስና መንዛዛት ፈጣን ፍትህ እንዳያግድ መጠንቀቅ ያስፈልጋል።

IV. ክስ አልመሰረትም ብሎ መወሰን/ክስ መዝጋት(38/መ/+42/1/ሀ-መ/

V. የምርመራ መዝገብ መዝጋት በ39(ሀ-ሐ/በተገለጹት ምክንያቶች

VI. ጠቅላይ ዐ/ህግ መሪ ጥዕዛዝ እንዲጠው መጠየቅ/አጠራጣሪ ሁኔታ ሲያጋጥም 41/ሃላፊነት ለማካፈል ፣ለመመካከር፣የዕውቀት ልውውጥን ያማከለ ነው/ ።አንቀጽ **39**ና **42** ን አነጻጽር

## ክስ አቀራረብ/አጻጻፍ/ክሱን በፍ/ቤት ስለማስተናገድ፣ክስን ማሻሻል

- ማንኛውም የወንጀል ክስ ለፍ/ቤት የሚቀርበው በዐ/ህግ በኩል ነው/ወ/ል/ህ/ቁ 211/። ዐ/ህግ የፖሊስ ምርመራ መዝገብ ተጠናቆ በደረሰው 15 ቀን ውስጥ ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት ክስ ማቅረብ አለበት(38/ሀ/+109)። የፍ/ቤቱን ሥልጣን ለመወሰን ዐ/ህግ የሥ/ሥ/ህ 1ኛ ሠንጠረዥ፣17/67፣25/88 እና እንዲሁም ልዩ ህጎች የተቀመጡትን የፍ/ቤት ሥልጣን (909-ህገ ወጥ ሰዎች ዝውውር እና ስደተኛ ድንበር ማሻገር፣652/2001ሽብር፣881/07ሙስና፣ ወዘተ) ያለውን በመረዳት ክሱን ለሚመለከተው ፍ/ቤት ማቅረብ አለበት።ሥልጣን ለሌለው ፍ/ቤት በስህተት ክስ ማቅረብ ,ተቀባይነት አይኖረውም(ሥ.110።ፍ/ቤትም የቀረበለት ክስ የማየት ስልጣን የሌለው መሆኑን ሲረዳ መቀበል የለበትም። በመሆኑም በክሱ ላይ የሚጠቅሰው ፍ/ቤት ስልጣን ያለው ስለመሆኑ ከሥ.99-107+110 አንጻር ማጣራት አለበት።
- በተለያየ ፍ/ቤት ሥልጣን ሥር ሊታይ የሚችል(ከፊል ከፍተኛ -ከፊል ደግሞ ዝቅተኛ ፍ/ቤት) ወንጀል በአንድ መዘገብ ላይ ሲኖር ክሱ መቅረብ የሚገባው አብዩ ወንጀሉን(ከፍ ያለውን ወንጀል )ለማየት ለሚችለው ነው(ሥ/ሥ/ህ 109/3/) ለምሳሌ፡ ደንብ መተላለፍ(809)እና 665፤ 539+665

# የክስ አጻጻፍ/ፎርምና ይዘት፣ስለ ክስ መቃወሚያና ማሻሻል

- ከደንብ መተላለፍ በቀር ክስ በጽሁፍ ፍ/ቤት ሳይቀርብ አይስናግድም፣ክስ የሚያቀርበው ዐ/ህግ ነው፣ፍ/ቤት ትዕዛዝ ሳይሰጥ አካለ መጠን ባላደረሰ ላይ ዐ/ህግ ክስ ማቅረብ አይችልም፣ክስ በህግ የተቀመጠ ፎርም መያዝ አለበት(ሥ.108
- የወንጀል ክስ ይዘትና ቅርጽ በህጉ መሰረት መሆን አለበት። የክስ ፎረም/ይዘት በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ **111 እና 112** የተገለፁትን ሁኔታዎች የሚያሙዋላና ከስ/ስ/ህግ ጋር ከተያያዘው 2ኛ ሰንጠረዥ በምሳሌነት ከሰፈረው የክስ አዘገጃጀት ጋር የተቀራረበ መሆን ይገባል።
- በወ/ህግ/ቁ/ 23 ላይ ወንጀልን የሚያቋቁሙ የህግ(legal element)፣የድርጊት (material element) ና የሃሳብ(moral element) ሁኔታዎች የተሟሉ መሆኑን ማረጋገጥ ና ክሱ ላይ ማሳየት ፣መግለጽ ይገባል። በወ/ህ/ቁ/24 መሰረት በምክንያትና ውጤት መካከል ግንኙነት ስለመኖሩ ማረጋገጥ ና ክሱ ላይ መግለጽ ይገባል።
- በየትኛው የህግ ድንጋጌ ስር ድርጊቱ ተሸፍኖ ክስ ሊያቀርብ እንደሚችል መለየት ያስፈልጋል።ለምሳሌ 560 vs.840,665 vs.852,665 vs669 የሚለውን በአግባቡ ታይቶ ከማስረጃውና ከድርጊቱ አንጻር መመር ያስፈልጋል።
- በሥ/ሥ 111/1/ሐ/ ሥር የተጠቀሰው ወ/ሉ የተፈጸመበት ቦታ፣ጊዜ(ዓ.ም፣ወር፣ቀንና ሰዓት)በዝርዝር በክሱ ላይ መጠቀስ አለበት። አንዳንዴ ወንጀሉ የተፈጸመበትን ጊዜ በርግጠኝነት ለማወቅ አዳጋች ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን ዓ.ም እና ወር ብቻ ቢታወቅ እና በዚህ መሰረት ክስ ቢቀርብ ውጤቱ ምን ይሆናል? ሁለት አመለካከት አለ 1/ ክሱ በህጉ አነጋገር ስላልቀረበ ውድቅ ሊደረግ ይገባል፣ ምክንያቱም የተከሳሹን የመከላከል ዕድል ስለሚያጠብ ነው 2/ክሱ ውድቅ ሊደረግ አይገባም። ምክንያቱም ጊዜ በተለያየ መንገድ ሊገለጽ ይችላል፣ጊዜው ሁሉም ተሙዋልቶ ባለመቅረቡ ብቻ ክሱን ከወዲሁ ውድቅ ከማድረግ ለክሱ የሚቀርበውን ማስረጃ አንጻር ሊመረመር ይገባል። የትኛው ሃሳብ የተሻለ ነው?

# የክስ አጻጻፍ/ፎርምና ይዘት.......

- ክሱ ከተመሰረተ በሁዋላ ያልታሰበ ስህተት ቢገኝ ይህ ብቻውን ክሱን ዋጋ አያሳጣውም፣ ነገር ግን ስህተቱ መሰረታዊ ከሆነ ወይም ሊያሳስተው የሚችል መሆኑ ከታመነበት ና በዚህ ምክንያት ትክክለኛ ፍርድ መስጠት የማይቻል ከሆነ ክሱን በማሻሻል ጉዳዩን መስማት ይቻላል።በመሆኑም በ118ና 119 መሰረት ክሱ መሻሻል(መለወጥ) አለበት። የማሻሻያ ምክንያቶቹ በከፊል የተከሳሽን ጥቀም የተመከቱ ናቸው።ክስ የሚሻሻለው ለተከሳሹ ተብሎ ሲሆን በተከሳሽ መቃወሚያ በ130 መሰረትም በመጀ/ደ/መቃወሚያነት ተነስቶ በፍ/ቤት ይስተናገዳል።
- የተሻሻለው ክስ ከቀድሞው ወንጀል ክስ ከፍ ያለ እንዲሆንና አዲስ ክስ ለመጨመር መሆን አይገባውም፣ምክንያቱም መሻሻሉ ተከሳሹን አይጠቅመውም።
- ተደደራራቢ ክሶች አቀራረብ በተመለከተም ጥንቃቄ ያስፈልጋል።ለምሳሌ ክስ 1፣ክስ 2፣ክስ 3...ወዘተ ተብሎ ይዘረዘራል።አንዳንድ ጊዜ በአንድ ክስ ተጠቃሎ ሊቀርብ የሚችለውን ከ 1 በላይ ክሶች በፍ/ቤት ሲቀርብ ይስተዋላል፤ ለምሳሌ 670+556+555(ውንብድና በራሱ ድብደባንም ይጨምራል፤ ስለዚህ ሌላ ከውንብድና ውጭ የሚጨመር ክስ አግባብ አይደለም)
- ቅጣት የሚያከብደውን ወንጀል ተጠቅሶ ክስ ሲቀርብ ሁኔታው መሙዋላቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ለምሳሌ 407/1/ vs 407/2/,689 vs 690,665 vs 669 ነገር ግን ተከሳሹ ቀድሞ የተቀጣበት የወንጀል ቅጣት በክሱ አይጠቀስም።
- በክሱ ላይ የማስረጃ አጠቃቀስ በተመለከተ የሰው፣የሰነድ፣የባለሙያ፣ኤግዚቢት፣ፎቶግራፍ፣ቪዴዮ ወዘተ ተብሎ ለጠቀስ ይችላል። ከዚህ ጋር በተያያዘ ማስረጃው ምን ለማስረዳት እንደተጠቀሰ ቢገለጽ ችሎቱ በቀላሉ እንዲረደው ያግዛል። አዋጅ ቁ.434/97 የሙስና ወንጀሎች ክስ ሲቀርብ ማስረጃው ሲጠቀስ የሚያስረዳው ጭብጥ መገለጽ እንዳለበት ያስገድዳል።
- መልመጃ ፡- የመደበኛ ዐ/ህግ ክስ እና የፀ/ሙ/ኮ/ ዐቃቤ ህግ ክስ አነጻጽሩ

# የክስ መስማት ሂደት

- ዐ/ህግ የተላከለትን የፖሊስ ምርመራ መዝገብ አጥንቶ ሲጨርስ ጉዳዩ ላይ ተጠርጣሪውን በፍ/ቤት ከሶ ጥፋተኛ ለማስባል በቂ ና አሳማኝ ማስረጃ መኖሩን ሲያምን ተከሳሽ የተላለፈውን የህግ ድንጋጌ በመለየትና በመጥቀስ ለክርክሩ መነሻ የሆነ ለፍ/ቤት ክስ ያቀርባል፡፡ ፍ/ቤት ከሁለቱ ተከራካሪዎች ገለልተኛ አካል መሆኑ ስለሚታመን ክሱን መርምሮ፣ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ተከሳሽን ጥፋተኛ በማለት ቅጣት ለመጣልም ሆነ ነጻ ለመልቀቅ ሥልጣን አለው፡፡በቅድሚያ ዐ/ህግ ክስ የሚያቀርብበት ፍ/ቤት ክሱን ተቀብሎ ማስረጃ ሰምቶ ውሳኔ ለመስጠት ሥልጣን ያለው ስለመሆኑ ማረጋገጥ ያለበት ሲሆን፣ በስህተት ያለስልጣኑ ቀርቦ ቢሆንም ፍ/ቤቱ በየትኛወም ጊዜ በራሱ አነሳሽነት አንስቶ እልባት ሊሰጥበት ይገባል፡፡ ምክንያቱም የፍ/ቤት ሥልጣን ጉዳይ በክርክር ሂደት ወሳኝ በመሆኑ ያለስልጣን የተሰጠ ፍርድ ቢኖር እንዳልተሰጠ ይቆጠርና ውድቅ ሊደረግ ስለሚችል ነው፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ያየው ፍ/ቤት ስለሥልጣን የተሳሳተ ቢሆንም በይግባኝ ፍ/ቤት ይስተካከላል**(rule of competency of crts.)**
- የሚቀርበው ክስ ላይ የሚጠቀሰው ወንጀል የየትኛው ፍ/ቤት ሥልጣን ስር እንደሚሆን በተለያዩ ህጎች ይወሰናል፡፡ ፍ/ቤት ክስ ሲቀርብለት በመጀመሪያ ትኩረት ሰጥቶ መመርመር የሚገባው ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ያለው ስለመሆኑ ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው፡፡

የፍ/ቤትን ሥልጣን ስለመወሰን

- በወንጀል ጉዳይ የሚሰጥ ፍርድ የሰዉን ዋና ዋና መብቶች የመቀነስ ዉጤት ስለሚኖረዉ ይህ በህግ በተሰጠ ሥልጣን መሰረት ሊከናወን ይገባዋል። ስለዚህ ክስ የቀረበለት ፍርድቤት የመጀመሪያ ተግባሩ የሚሆነዉ ነገሩን ለመዳኘት ሥልጣን ያለዉ መሆኑን መወሰን ነዉ። በዚህ ረገድ ክሱን የሚያቀርበዉ ዐቃቤህግም የሚጫወተዉ የራሱ ሚና አለዉ።
- በተለይም ወንጀል በተለያየ የዓለም አካባቢ ሊፈጸም የሚችል እንደመሆኑ በተለያየ ምክንያት ከአንድ ሃገር በላይ በነገሩ ላይ ሥልጣን አለኝ ብሎ ሊፈርድ ስለሚችል የየትኛዉ ሃገር ፍርድቤት ሥልጣን እንዳለዉ፣ የዚህ ሀገር /ኢትዮጵያ በምትሆንበት ጊዜ/ የትኛዉ ፍርድቤት በተለይ ነገሩን የመዳኘት ሥልጣን እንደተሰጠዉ መወሰን ለተሰጠዉ ፍርድ ተቀባይነት ማግኘት ወይም ለህጋዊነቱ ቁልፍ መመዘኛ ነዉ። ይህ ሁሉ የሥልጣን ነገር በተለያዩ ህግጋት የተወሰነ ስለሆነ እነዚህን ህግጋትና አተገባበራቸዉን በዚህ ክፍል በሚቀርበዉ ሥልጠና እንመረምራለን።

# የፍ/ቤትን ሥልጣን ስለመወሰን

- ፍርድ ቤቶች አንድ ክስ ከቀረበላቸው በኋላ በቅድሚያ ትኩረት ሰጥተው ማየትና ማረጋገጥ ያለባቸው ጉዳይ ቢኖር ክሱን ለማየት ስልጣን ያላቸው መሆን አለመሆኑን ነዉ። በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ ዳኞች ጉዳዩን የማየት ስልጣን ያላቸው መሆኑን ሳያረጋግጡ ነገሩን መስማት የለባቸውም። ወንጀል የሚፈጸምበት ቦታ የትኛዉም የዓለም ክፍል ሊሆን ስለሚችል የአንድ ሃገር ፍርድቤት በዚህ ጊዜ ስለሚኖረዉ ሥልጣን መወሰን አስፈላጊ ነዉ። የአንድ ሃገር ፍርድቤቶች በዚሁ ሀገር በተፈጸሙ ወንጀሎች ላይ ብቻ ሳይሆን በሌላ ሃገር በተፈጸመ ወንጀልም ሥልጣን ሊኖራቸዉ ይችላል። ከዚህ አኳያ በጠቅላላዉ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ወንጀሎችን በሚመለከት ያላቸው ስልጣን ሁለት ባህሪያቶች ይዞ ይገኛል፡፡
- የመጀመሪያዉ የኢትዮጵያ የወንጀል ህግ ተፈጻሚ በሚሆንባቸዉ ወንጀሎችና አጥፊዎች ምንነትና ማንነት ላይ የተመሰረተ ነዉ። የኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ ተፈጻሚ የሚሆንባቸዉ ሰዎች ላይ ሁሉ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ስልጣን አላቸው፡፡ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ስልጣን ስር የሚወድቁ ሰዎች እና ወንጀሎች ጉዳይ በወንጀል ሕግ ከቁ 11 እስከ 20 ተዘርዝሮ ይገኛል፡፡
- ሁለተኛዉ ሁኔታ ደግሞ ከላይ በተመለከተዉ አይነት በተገኘዉ ሥልጣን መሰረት የትኛዉ የኢትዮጵያ ፍርድቤት ሥልጣን ይኖረዋል ከሚለዉ ጥያቄ ጋር የተያያዘ ነዉ። ይህም ፍርድቤቶች በቦታና በደረጃ የተዋቀሩ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የሚወሰን ነዉ። የት ቦታ ያለ የትኛዉ ደረጃ ፍርድቤት ጉዳዩን ሊሰማ ይችላል በሚለዉ መሰረት የተለያዩ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች የወንጀል ጉዳይን ለማየት ያላቸው ስልጣን ይወሰናል። ይህ ጉዳይ በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ 4፣6፣7 እና ከ99-107 በተደነገጉት የሚመራ ነዉ፡፡ ከዚህም በቀር አሁን ባለዉ የፌዴራልና የክልል መንግሥት አወቃቀር ምክንያት በሁለቱ መንግሥታት ፍርድቤቶች መካከል የሥልጣን ክፍፍል ስላለ ይህን ክፍፍል በሚደነግጉ ህግጋት መሰረት ሥልጣናቸዉ ይወሰናል /ህገመንግሥትና የፌዴራል ፍርድቤቶች አዋጆች ሊጠቀሱ ይችላሉ/።

## የፍ/ቤትን ሥልጣን ስለመወሰን

- ስለዚህ ዐቃቤ ህግ ክስ በሚመሰርትበት ጊዜ እነዚህን የኢትዮጵያ ፍርድቤቶች ሥልጣን ሁኔታዎች አጣርቶ መሆን ይኖርበታል። በቅድሚያ ነገሩ ከኢትዮጵያ ዉጪ የሆነ ነገርን ያካተተ ከሆነ የኢትዮጵያ ፍርድቤቶች በነገሩ ላይ ሥልጣን ያላቸዉ መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል።ሥልጣኑ እንዳላቸዉ ካረጋገጠ ደግሞ የትኛዉ ፍርድ ቤት /የክልል ወይስ የፌዴራል፣ ከፍተኛ ወይስ የመጀመሪያ ደረጃ/ ሥልጣን እንዳለዉ ለይቶ ክሱን ማዘጋጀት ይጠበቅበታል።
- ፍርድ ቤቶችም ክስ ሲቀርብላቸዉ እነዚህ ሥልጣኖች ያላቸዉ መሆን አለመሆኑን ካጣሩ እና ካረጋገጡ በኋላ ነገሩን ወደማየት መግባት መቻል አለባቸዉ። ይህን ነገር ተከራካሪዎች እስኪያስታዉሷቸዉ መጠበቅ የለባቸዉም። ክስ እንደቀረበ ተከራካሪዎችን ከመጥራታቸዉ በፊት የመጀመሪያ ተግባራቸዉ መሆን ያለበት በነገሩ ላይ ሥልጣን ያላቸዉ መሆኑን መለየት ነዉ።
- ዐቃቤህግ ከላይ የተመለከትነዉን ግዴታዉን ሳይወጣ ቀርቶ ክሱን ሥልጣኑ ላልሆነ ፍርድቤት ሊያቀርብ ይችላል። በዚህ ጊዜ ፍርድቤት ክሱን ተቀብዬ አላስተናግድም ማለት አለበት። ዐቃቤህጉንም ክሱን ሥልጣን ላለዉ ፍርድቤት እንዲያቀርብ በክስ ማመልከቻዉ ላይ ሊያዝዘዉ ይገባል /የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 110/።

# የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ሥልጣን /የኢትዮጵያ የወንጀል ህግ ተፈጻሚ የሚሆንባቸዉ ጉዳዮችና ሰዎች/

- አንድ ሰው የኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ ተፈጻሚ የሚሆንበት መሆን አለመሆኑን ለመወሰን የሚያስችሉት፣
- ሀ) ወንጀሉ የተፈፀመበት ቦታ፣
- ለ) የተከሳሹ ወይም የተጎጂዉ ዜግነት፣ እና
- ሐ) የተፈፀመው ወንጀል ዓይነት ናቸው። እነዚህ ነገሮች ደግሞ ኢትዩጵያ በጉዳዩ ላይ የሚኖራትን ሥልጣን **ዋና ስልጣን(Principal Jurisdiction)** ወይም **ምትክ (አነስተኛ) ሥልጣን (Subsidiary Jurisdiction)**እንዲሆን ሊያደርጉት ይችላሉ።
- **ዋና ሥልጣን (Principal Jurisdiction)፡** የኢትዮጵያ ፍርድቤቶች በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ዋና ስልጣን አላቸዉ። ሀ) ኢትዮጵያ ውስጥ በተፈፀመ ወንጀል፣ ለ) በውጭ አገር በኢትዮጵያ ጥቅም ላይ በተፈጸመ ወንጀል፣ ሐ) የማይደፈር ወይም ያለመከሰስ መብት ያለዉ ኢትዮጵያዊ በውጭ አገር በፈጸመዉ ወንጀል፣ እና መ) የኢትዮጵያ መንግስት የመከላከያ ሰራዊት አባል በውጭ አገር በፈጸመዉ ዓለም አቀፍ ወይም ወታደራዊ ወንጀል
- **ሀ) ኢትዮጵያ ውስጥ ስለተሰሩ ወንጀሎች(ወ/ል/ሀ 11-12)፡** የወ/ህ/ቁ/ 11(1) በወንጀል ሕግ ከተጠቀሱት ማንኛውንም ወንጀል በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ የሰራ ማንኛውም ሰው በዚሁ ሕግ መሰረት እንደሚቀጣ ይገልፃል:: (ግዛት ሲባል የብስና አየርም ይጨምራል)። ስለዚህ እንዲህ አይነት ወንጀሎችና ፈጻሚዎቻቸዉ በኢትዮጵያ ፍርድቤቶች ሥልጣን ስር ናቸዉ፣ በየትም ሃገር ተከሰዉ ቢቀጡ በኢትዮጵያ ተከሰዉ ከመቀጣት አይድኑም። **ለምሳሌ** አንድ የግብፅ ዜጋ ለጉብኝት ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ የወንጀል ሕግ ቁ 620 በመተላለፍ በሌላ ግብፃዊት ላይ የአስገድዶ መድፈር ወንጀል ፈፅሞባታል ቢባል ወንጀሉ የተፈፀመው በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ በመሆኑ ተከሳሹ በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ ይዳኛል:: ስለዚህ የወንጀል ሕግ ቁ 620 ጥሰሃል ተብሎ ሥልጣን ባለዉ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤት ተከስሶ ሊፈረድበት ይችላል::

## የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ሥልጣን…ዋና ሥልጣን ኢትዮጵያ ውስጥ ስለተሰሩ ወንጀሎች

- በወ/ህ/ቁ/ 11(3) እንደተመለከተው አንድ ሰው ኢትዮጵያ ውስጥ ወንጀል ሰርቶ ከኢትዮጵያ አምልጦ በሌላ አገር ጥገኝነት ጠይቆ ቢቀመጥ የኢትዮጵያ መንግስት ወንጀለኛውን በጥገኝነት ያስቀመጠው መንግስት አሳልፎ እንዲሰጠው ለመጠየቅ ይችላል:: የኢትዮጵያ መንግስት ይህን ጥያቄ ማቅረብ የሚችለው ግን የዚህ ዓይነት ስምምነት ጥገኝነትን ከሰጠች አገር ጋር ያለው እንደሆነ ነው:: ስምምነት ከሌለ ወይም አሳልፎ መስጠቱ ያልተፈቀደ ከሆነ ጥገኝነት በሰጠዉ አገር እንዲከሰስና እንዲፈረድበት ኢትዮጵያ ዉክልና መስጠት ትችላለች:: በዚህ ዉክልና መሰረት የሚከናወነዉ ሁሉ በኢትዮጵያ እንደተከናወነ ይቆጠራል፡፡ ስለዚህ በዚህ መሰረት በዛው አገር ተከስሶ ነፃ የተባለ እንደሆነ፣ ምሕረት ወይም ይቅርታ ተደርጎለት እንደሆነ ወይም ክሱ ወይም ቅጣቱ በይርጋ ምክንያት ተሰርዞለት እንደሆነ ኢትዮጵያ ውስጥ ገብቶ ቢያዝም ሊከሰስና ሊቀጣ ኣይቻልም (የወ/ህ/ቁ/ 12(2):: ወንጀሉ በኢትዮጵያ የተፈጸመ ቢሆንም በዉጭ ሃገር የተከናወነዉ ሂደት በዉክልና የተካሄደ በመሆኑ አስገዳጅነት ይኖረዋል፡፡
- ሆኖም የኢትዮጵያ መንግስት ተጠርጣሪው ጥገኝነት በጠየቀበት አገር ውስጥ እንዲከሰስ አስጠጊውን አገር ባይጠይቅና አስጠጊው መንግስት ራሱ ከስሶ በነፃ ቢለቀውና በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ቢመጣ እንደገና በኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች ተከስሶ ሊፈረድበት ይቻላል (የወ/ህ/ቁ/ 16(2)):: ሌላዉ ሃገር ሂደቱን ያከናወነዉ በራሱ እንጂ ኢትዮጵያን ወክሎ ስላልሆነ ሂደቱና ዉጤቱ በኢትዮጵያ ላይ አስገዳጅነት የለዉም፡፡

- በሌላ በኩል ይህ ሰዉ በኢትዮጵያ ዉክልና መሰረት በውጭ አገር ተፈርዶበት ቅጣቱን ሳይፈፅም ወይም በከፊል ብቻ ፈፅሞ ወደ ኢትዮጵያ ቢገባ ያልተፈፀመው ቅጣት በኢትዮጵያ ይፈፀማል (የወ/ህ/ቁ/ 12(3)):: ቅጣቱ ተፈፃሚ የሚሆነው ግን በይርጋ እስካልታገደ ድረስ ነው::

- **ለ/ በውጭ ሀገር ሆኖ በኢትዮጵያ ላይ ስለሚሰሩ ወንጀሎች(ወ/ል/ህ 13፡** ይህ ድንጋጌ የሚመለከተው በኢትዮጵያ መንግስት በደህንነቱ ወይም አንድነቱ ላይ በሕጋዊ ተቋማቱ ወይም ዋና ዋና ጥቅሞቹ ወይም በገንዘቡ ላይ ወንጀል ባደረገ በማናቸውም ሰው ላይ ተፈፃሚ የሚሆን ነው:: እነዚህ ወንጀሎች በወንጀል ሕግ ቁ 238 - 260 እና 355 - 374 ስር የተመለከቱት ናቸው:: ለምሳሌ:- አንድ የውጭ አገር ዜጋ በውጭ አገር ካሉ ኢትዮጵያውያን ጋር በመሆን የኢትዮጵያ መንግስትን ለመገልበጥ **ውጭ አገር ሆኖ ቢያድምና ይህንኑ አድማ** ለማከናወን የሐሰት ገንዘብ (በኢትዮጵያ ገንዘብ መልክ) ቢያሳትም ወንጀሉ የወ/ህ/ቁ 238 እና 357 ስለሚጥስ በወ/ህ/ቁ 13 መሰረት ኢትዮጵያ በጉዳዩ ላይ ዋና ስልጣን ይኖራታል::
- **ሐ) የማይደፈር መብት ያለው ኢትዮጵያዊ እና የኢትዮጵያ መንግስት የመከለከያ ሰራዊት አባል በውጭ አገር ሆኖው የሚያደርጉዋቸው ወንጀሎች (የወ/ህ/ቁ 14 እና 15**)፡ በውጭ አገር ያሉ የማይደፈር መብት ያላቸዉ የኢትዮጵያ መንግስት ወኪሎች የሚፈጽሟቸዉ ወንጀሎች ሁሉ በኢትዮጵያ ፍርድቤቶች ዋና ስልጣን ስር ናቸው:: የማይደፈር መብት ያላቸው ኢትዮጵያዊያን በውጭ አገር በፈፀሙት ወንጀል ምክንያት በኢትዮጵያ ዋና ስልጣን ስር ሊወድቁ የሚችሉት ወንጀሉ በኢትዮጵያ እና ወንጀል በተፈፀመበት አገር ሕግ የሚያስቀጣ ከሆነ ነው::
- **መ**)በውጭ አገር ያሉ የኢትዮጵያ መንግስት መከላከያ ሰራዊት አባላትም የሚፈጽሟቸዉ የተለዩ ወንጀሎች እንደዚሁ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ዋና ስልጣን ስር ናቸዉ። የመከላከያ ሰራዊት አባል በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ ከቁ. 269 እስከ 322 የተጠቀሱትን ወንጀሎች በመስራት የዓለም አቀፍ ሕግን የጣሰ ወይም ወታደራዊ ጠባይ ያለውን ወንጀል የሰራ እንደሆ በኢትዮጵያ ዋና ስልጣን ስር ሆኖ በጦር ፍርድ ቤት ክሱ ይታያል::

# የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ሥልጣን…ምትክ ሥልጣን

- የምትክ ስልጣን ሃሳብ ተፈጻሚ ሊሆን የሚችለዉ ተሰራ የተባለው ወንጀል ኢትዮጵያን በዋናነት የማይነካ ወይም የማይጎዳ ሲሆን ነው። የሚከተሉት ወንጀሎች በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ምትክ ስልጣን ስር የወንጀል ህጉ የሚፈጸምባቸዉ ናቸው፡፡ ወንጀሎቹም እስካሁን ካየናቸዉ ወንጀሎች ዉጪ የሆኑ ናቸዉ። ሀ) በውጭ አገር የተፈጸመ ዓለም አቀፍ ሕግን የሚጥስ ወይም የህዝብን ጤንነትና ሞራል የሚጎዳ ወንጀል፣ ለ) በውጭ አገር በኢትዮጵያ ዜጋ ላይ የተፈጸመ ወንጀል፣ ሐ) በዉጭ ሃገር በኢትዮጵያዊ ዜጋ የተፈጸመ ወንጀል፣ መ/ በውጭ አገር በማንኛውም ሰው ላይ በዉጭ ሃገር ሰዉ የተፈጸመ ከባድ ወንጀል/በኢትዮጵያ የወንጀል ህግ ከአስር ዓመት ባላነሰ ጽኑ እስራት ወይም በሞት ሊያስቀጣ የሚችል ወንጀል/፣ ወይም ሠ/ በውጭ አገር በሚገኝ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት አባል የዚህን አገር ተራ ሕግ በመጣስ የተፈጸመ ወንጀል ናቸው። እንደሚታየዉ የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች በምትክ ሥልጣን የሚዳኟቸዉ ወንጀሎች በዉጭ ሃገር የተፈጸሙ መሆን ይገባቸዋል።

# የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ሥልጣን…ምትክ ሥልጣን

- *1.* **በዓለም አቀፍ ሕግና ስርዓት ላይ ከኢትዮጵያ ውጭ የሚደረጉ ወንጀሎች (የወ/ህ/ቁ 17) እና በወ/ህ/ቁ 14 እና 15(2)** ከተደነገጉት ሁኔታዎች ውጭ በወ/ህ/ቁ 17 የተጠቀሱት ወንጀሎች ሲፈጸሙ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ምትክ ስልጣን ስር የወንጀል ህጉ ይፈጸምባቸዋል:: ይህም የሚሆነዉ ወንጀሉ በተፈጸመበት ሃገር በዚህ ወንጀል ላይ ክስ ሳይቀርብና ፍርድ ሳይሰጥ ከቀረ ነዉ።
- በውጭ አገር ዓለም አቀፍ ሕግን የጣሰ ወይም በኢትዮጵያ ሕግ ዓለም አቀፍ ወንጀል ነው ተብሎ የተደነገገውን ወንጀል የፈፀመ ወይም ኢትዮጵያ በተስማማችበት ዓለም አቀፍ ስምምነት ወንጀል ነው ተብሎ የተወሰነውን የፈፀመ ማነኛውም ሰው በኢትዮጵያ ምትክ ስልጣን ስር ነው:: ዓለም አቀፍ ወንጀሎች ከወ/ህ/ቁ 269 እስከ 283 የተዘረዘሩት ሲሆኑ ፣ ሌሎቹ ከላይ የተጠቀሱት ወንጀሎች ደግሞ በነጋሪት ጋዜጣና ኢትዮጵያ አባል በሆነችባቸው ወንጀል ጠቀስ በሆኑ ስምምነቶች ውስጥ የሚገኙ ናቸው:: በተጨማሪም የህዝብን ጤንነት ወይም ሞራል የሚጎዱ ወንጀሎችን በውጭ አገር የፈፀሙ ሰዎች በኢትዮጵያ ምትክ ስልጣን ስር ናቸው:: እነዚህም ወንጀሎች በወ/ህ/ቁ 525 (መርዛማ ወይም የናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድሐኒቶችን ወይም ዕፆችን ማምረት፣ መስራት፣ ማዘዋወር ወይም መጠቀም)፣ በወ/ህ/ቁ 599፣ 635፣ 636፣ 640፣ 641 የተመለከቱት ናቸው::

# የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ሥልጣን...ምትክ ሥልጣን

- **2. ከኢትዮጵያ ውጭ የሚደረጉ ሌሎች ወንጀሎች (የወ/ህ/ቁ 18)**
- **ሀ)** በዚህ ድንጋጌ መሰረት አንድ ወንጀል በኢትዮጵያ ምትክ ስልጣን ስር የሚሆነው፣ በኢትዮጵያ ዜጋ ላይ ወይም በማንኛውም የኢትዮጵያ ዜጋ ከኢትዮጵያ ውጭ የተፈጸመ በወ/ህ/ቁ 11-17 ከተገለፁት ዉጪ የሆነ ወንጀል ከሆነና በዚሁ ወንጀል በውጭ አገር ክስ ሳይቀርብና ፍርድ ሳይሰጥ ከቀረ ነዉ:: ይህን ለማድረግ ግን:- **1)** ድርጊቱ በተፈፀመበት አገር ሕግና በኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ የሚያስቀጣ መሆኑ ተደንግጎ እንደሆነ፣ እና **2)** የተፈፀመው ወንጀል ከባድ በመሆኑ በኢትዮጵያ ሕግ መሰረት ተከሳሹ ተይዞ ተላልፎ እንዲሰጥ ለማድረግ በቂ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ነው። **ለምሳሌ:-** "ሀ" እና "ለ" የተባሉ ሁለት አገሮች አሉ እንበል:: ከ "ለ"ጋር ኢትዮጵያ ተራ የሆነ የሰው ግድያ ወንጀል የፈፀመ ሰው አሳልፎ ይሰጣል የሚል ስምምነት አላት:: ከ"ሀ" ጋር ግን ይህ ስምምነት የላትም። በዚህ መሰረት አንድ የ "ለ" አገር ተወላጅ በ "ሀ" አገር አንዱን ኢትዮጵያዊ ቢገድለው ይህም በ "ሀ" አገር ሕግና በኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ (የወ/ህ/ቁ 540) ወንጀል ስለሆነ ገዳዩ በኢትዮጵያ ምትክ ስልጣን ስር ይሆናል:: ምክንያቱም፣ 1) ወንጀሉ የተፈፀመው በኢትዮጵያ ዜጋ ላይ በመሆኑ ፣2) ወንጀሉ በኢትዮጵያም በ "ሀ" ም አገር ሕግ መሰረት የሚያስቀጣ በመሆኑ ፣እና 3) ወንጀሉ በኢትዮጵያ ሕግ መሰረት አሳልፎ ለመስጠት በቂ ከባድነት ያለው በመሆኑ /ምክንያቱም ኢትዮጵያ በዚህ ወንጀል አሳልፎ የመስጠት ስምምነትዉስጥ ገብታለችና/ ነው::

# የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ሥልጣን...ምትክ ሥልጣን

- **ለ)** በዉጭ ሃገር ወንጀል ፈጽሞ ወደ ኢትዮጵያ የገባ የውጭ አገር ሰው በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ምትክ ሥልጣን ይዳኛል። ይህ የሚሆነዉ በኢትየጵያ ሕግ መሰረት ተላልፎ ካልተሰጠ ወይም በሌላ አኳኋን ካልተደነገገ እና ወንጀሉ ከአስር ዓመት ባላነሰ ፅኑ እስራት ወይም በሞት ሊያስቀጣ የሚችል ሲሆን ነዉ (የወ/ህ/ቁ 18(2))::
- **3. ከኢትዮጵያ ውጭ የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት አባል ስለሚሰራው ወንጀል (የወ/ህ/ቁ 15(1)፡-**
- ማንም የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት አባል በውጭ አገር መደበኛ ሕግን በመጣስ የሚፈጽመዉ ወንጀል በኢትዮጵያ ፍርድቤቶች ምትክ ስልጣን ስር ይዳኛል:: ወንጀል በተፈፀመበት አገር ተይዞ ሊከሰስና ሊፈረድበት ይችላል:: ሸሽቶ ወደ ኢትዮጵያ የመጣ እንደሆነ ደግሞ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ምትክ ሥልጣን ስር በወንጀል ህጉ ይዳኛል (የወ/ህ/ቁ 15/1/፣ 21(2)):: በወ/ህ/ቁ 19(4) እንደተመለከተው አንድ ሰው በውጭ አገር ወንጀል ሰርቶ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ምትክ ስልጣን ስር የሚከሰስ ቢሆን የውጭ አገሩና የኢትዮጵያ የወንጀል ሕጎች በሚደነግጉት ቅጣት መካከል ልዩነት ያለ እነደሆነ ተፈፃሚ የሚሆነው አነስተኛዉ ወይም ቀላሉ ቅጣት ይሆናል:: ለምሳሌ ወንጀሉ በተሰራበት አገር በዕድሜ ልክ የሚያስቀጣ በኢትዮጵያ ሕግ ግን በሞት የሚያስቀጣ ቢሆን የኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች ተፈፃሚ የሚያደርጉት የዕድሜ ልክ እስራት የሚያዘውን የሌላዉን ሃገር ሕግ ይሆናል ማለት ነው:: ይህ ሰው በውጭ አገር ተከስሶ ነፃ ከወጣ ወይም አያስከስሰውም ከተባለ እንደገና ኢትዮጵያ ውስጥ እንደማይከሰስ ከሕጉ መገንዘብ ይቻላል (የወ/ህ/ቁ 20(1)):: ይህን ሥልጣን ኢትዮጵያ ልትሠራበት የምትችለዉ ወንጀሉ በሌላ ሃገር ባለሥልጣን ክስ ሳይቀርብበትና ፍርድ ሳይሰጥበት ከቀረ ነዉ። ምትክ ሥልጣን የሚያስብለዉም ይኸዉ ነዉ።

# የፌደራልና የክልል ፍ/ቤቶች ሥልጣን

- ከዚህ በፊት ባለዉ ክፍል ባየነዉ አይነት የኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች ሥልጣን ሲያገኙ በአህሪቱ ካሉት እጅግ በርካታ ፍ/ቤቶች የትኛዉ ነገሩን ለመዳኘት ሥልጣን እንደሚኖረዉ ሊወሰን ይገባል። አሁን በሃገሪቱ ባለዉ የፍ/ቤቶች አወቃቀር መሰረት ሊወሰን የሚገባዉ የመጀመሪያዉ የሥልጣን ጥያቄ ከፌዴራል እና ከክልል መንግስታት ፍ/ቤቶች የትኛዉ ፍ/ቤት ሥልጣን ሊኖረዉ እንደሚችል ነዉ። የክልል ፍ/ቤቶች ስልጣን በየክልሉ ብቻ የተወሰነ ነዉ። የፌዴራል ፍ/ቤቶች ስልጣን ግን በአ/አበባና ድሬዳዋ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን በጉዳዮች ዓይነት ተለይቶ ወደ ሁሉም ክልሎች ሊደርስ ይችላል።
- የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ ኣዋጅ ቁጥር 25/88 /በአዋጅ ቁ/ 138/1991፣ 321/95 እንደተሻሻለዉ/ በዓንቀፅ 4 ላይ የፌዴራል ፍ/ቤቶች በወንጀል ጉዳይ ያላቸው ስልጣን ተደንግገ ይገኛል። በዚህ ዓንቀፅ ላይ የተዘረዘሩት ወንጀሎች በየትኛውም ክልል ተፈፅመው ሲገኙ ጉዳዮቹን ኣይተው የመወሰን ስልጣን ያላቸው የፌዴራል ፍ/ቤቶች ናቸው። ያም ሆኖ ግን በፌዴራል ፍ/ቤቶች ስልጣን ስር የሚወድቁ ሆነው በክልሎች ውስጥ የሚፈፀሙ የወንጀል ጉዳዮች የክልል ፍ/ቤቶች **በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 78 (2) ባገኙት ውክልና** መሰረት ከራሳቸው ስልጣን በተጨማሪ የፌዴራል ፍ/ቤቶች ስልጣን የሆነውን የወንጀል ጉዳይም ደርበው ያያሉ።
- በአዋጅ ቁ 25/1988 እና በማሻሻያዎቹ አዋጅ ቁ 138/1991 እና 321/1995 መሰረት የፌዴራል ፍ/ቤቶች በወንጀል ጉዳዮች ላይ ያላቸውን ስልጣን እንደሚከተለው ማስቀመጥ ይቻላል። ከ1-14 የተዘረዘሩትን ፌደራል ፍ/ቤቶች ብቻ(exclusive jurisdiction) ያያሉ, በተጨማሪም 652/2001 ፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ መሰረት ክሱ ቀርቦ የሚያዩት ፌደራል ፍ/ቤቶች ናቸው።ከነኝህ ውጭ ያሉት ወንጀሎች በክልል ተፈጽመው ቢገኙ ከክልል ፍ/ቤቶች ሥልጣን ውጭ አይሆኑም ማለት ነው።

# ፌደራልና ክልል ፍ/ቤት ሥልጣን....

- እነዚህ ወንጀሎች ሁሉም በወንጀል ህጎች የተደነገጉ ወንጀሎች ናቸዉ። እነዚህም በዋናነት በፌዴራል መንግሥት ህግ አዉጪ ባለሥልጣን የሚወጡ ናቸዉ። በህገመንግሥቱ እንደተመለከተዉ የወንጀል ህግጋትን የማዉጣት ሥልጣን የፌዴራል መንግሥት ህግ አዉጪ አካል ነዉ። በነዚህ ህጎች ያልተሸፈኑ ጉዳዮች ካጋጠሙ የክልል መንግሥታት የወንጀል ህግ ሊያወጡ ይችላሉ። በነዚህ የክልል የወንጀል ህግጋት መሰረት ዳኝነት የሚሰጡት ፍርድ ቤቶች ደግሞ የክልሉ ፍርድ ቤቶች መሆን ይኖርባቸዋል። የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን የሚመለከቱ ህግጋት የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን ያላቸዉ በፌዴራል መንግሥት በወጡ ህግጋት መሰረት ወንጀል በሆኑ ጉዳዮች ላይ ነዉ ይላሉ /አዋጅ ቁ 25/1988 ቁ 3 ይመለከቷል/። ስለዚህ ለፌዴራል ፍርድቤቶች ከተሰጡት ሥልጣኖች ዉጪ በሆኑ ወንጀሎችና በክልል ህግጋት በተደነገጉ ወንጀሎች ጉዳይ ሥልጣን የሚኖራቸዉ የክልል ፍርድቤቶች ናቸዉ።
- **1.2.1 የሥረነገር ሥልጣን:-** ከፌዴራልና ከክልል የትኛዉ ፍርድቤት ሥልጣን እንዳለዉ ከተወሰነ በኋላ የዚህ ፍርድቤት የትኛዉ ደረጃ ላይ ያለ ፍርድቤት /የመጀመሪያ ደረጃ/የወረዳ  ፍርድ ቤት፣ የዞን/ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይስ ጠቅላይ ፍርድ ቤት/ ነገሩን ለማየት ሥልጣን እንዳለዉ ይወሰናል። ይህም የሥረ-ነገር ሥልጣን የሚባለዉ ነዉ።  የፌዴራል ፍርድቤቶች ሥልጣን በመጀመሪያ ደረጃ፣ በከፍተኛና በጠቅላይ ፍርድቤት ደረጃዎች የተዋቀረ ሲሆን የክልል ፍርድ ቤቶችም ሥልጣን በተመሳሳይ ሁኔታ በወረዳ፣ በዞንና በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተከፋፈለ ነው። አንዳንድ ክልሎች ቀላል የወንጀል ጉዳዮችን በማህበራዊ ፍርድ ቤት እንዲዳኙ ስልጣን የሰጡበት ሁኔታም አለ።

# ሥረ ነገር ሥልጣን

- የወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ. 4 ፍርድ ቤቶች የሚያዩዋቸውና የሚፈርዱባቸው በዚሁ የስነ ስርዓት ሕግ በአንደኛው ሰንጠረዥ መሰረት እንደሆነ ያዝዛል፡፡ ይህ ሰንጠረዥ ግን ሕጉ ሲወጣ በነበረው የፍርድ ቤቶች አወቃቀር መሰረተ የተዘጋጀ መሆኑን መርሳት የለብንም፡፡ በአሁኑ ጊዜ የፍርድ ቤቶች ስልጣን በሚመለከት አንዳንድ ለውጦች ተደርገዋል፡፡ ከነዚህ ለውጦች አንዱ ደግሞ ድሮ በአውራጃ ፍርድ ቤት ይታይ የነበረ የወንጀል ዓይነት በአሁኑ ጊዜ የአውራጃ ግዛት ክፍፍል ስለሌለ ለወረዳ ፍርድ ቤት መሰጠቱ ነዉ፡፡ እንዲሁም በፌደራልና በክልል ፍርድ ቤቶች የሚታዩ ወንጀሎች ተለይተው ተቀምጠዋል፡፡የተሰራው ወንጀል በወንጀል ሕግ ሳይሆን በሌላ ህግ የተደነገገ ቢሆን የትኛው ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ ስልጣን እንዳለው የሚወስነው ለጥፋቱ የተመደበውን ከፍተኛ የቅጣት ወሰን በመመልከት ነው፡፡ ይህም በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ 1ኛ ሰንጠረዥ መጨረሻ ላይ እንደተመለከተዉ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ይህ ሰንጠረዥ በዚሁ ህግ በቁ 4/2/ በተደነገገዉ መሰረት የፍርድ ሚኒስትሩ በህግ ማስታወቂያ ቁ 17/1967 ባወጣዉ ደንብ ያሻሻለዉ ስለሆነ በዚሁ መሰረት የሚገዛ ነዉ፡፡ ከተሻሻሉት ነገሮች አንዱ ከወንጀል ህጉ ዉጪ በሌላ ህግ የተደነገጉትን ወንጀሎች የቅጣታቸዉን መጠን በመመርኮዝ ነገሩ በየትኛዉ የፍርድቤት ደረጃ እንደሚታይ በሰንጠረዡ ተመልክቶ የነበረዉን ይመለከታል፡፡
- ፍርድ ቤቶች ይግባኝ ለማየት ያላቸው ስልጣን በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ.182 መሰረት እንደሆነ የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ሥ/ቁ 7 ይደነግጋል፡፡ ሆኖም አዲስ የመንግስት አወቃቀር ከተደረገ በኋላ በዚህ ዙሪያ ለውጦች ተደርገዋል፡፡ ከላይ እንደተመለከተዉ በአንዳንድ ክልሎች ከወረዳ ፍርድቤት በታች በአንዳንድ የወንጀል ባህሪ ባላቸዉ ጉዳዮች ላይ ሥልጣን ያላቸዉ ፍርድቤቶች ተቋቁመዉ ይገኛሉ፡፡ ከነዚህ ፍርድቤቶች ዉሳኔ የሚነሳ ይግባኝ የመስማት ሥልጣን ለወረዳ ፍርድቤቶች ተሰጥቶ ይገኛል /ቤንሻንጉል ጉምዝ፣ ትግራይ፣ አዲስ አበባ/፣ የወረዳ ፍርድቤቶቹ ዉሳኔዎችም የመጨረሻ ናቸዉ፡፡

# አካባቢያዊ ሥልጣን

- ኣንዳንድ ተግባሮች ደግሞ ከወንጀል ስራዎች ጋር ባላቸው ግንኙነት ምክንያት ወንጀል ይሆናሉ። ቀጥሎ የሚነሳዉ ጉዳይ ደግሞ ወንጀሉ ከበርካታ ቦታዎች በየትኛዉ እንደተፈፀመ ለማወቅ የማይቻል ሲሆን፣ በበርካታ ቦታዎች የተፈጸመ ሲሆን ክስ መሰማት ያለበት የት ነው የሚለውን ነው። ለዚህ ጥያቄም የወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ. 102 ያስቀመጠው መፍትሄ አለ። በአንቀፁ እንደተመለከተው ወንጀሉ ከበርካታ ቦታዎች መካከል የት እንደተፈፀመ ለማወቅ የማይቻል ሲሆን፣ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ቦታዎች የተፈጸመ ሲሆን ክሱ ከነዚህ ቦታዎች በአንዱ ስፍራ በሚገኝ የሥረነገር ሥልጣን ባለዉ ፍርድ ቤት ሊቀርብ ይችላል። ለምሳሌ ተከሳሹ በምስራቅ ሸዋ ዞን ሆኖ በምዕራብ ሸዋ ዞን ላለ ሰው የያዝከው ግመል የእኔ ነዉ በማለት የሐሰት ደብዳቤ ይፅፍለታል። ቀጥሎም ወደ ምዕራብ ሸዋ ዞን ሄዶ በማታለል ግመሉን ይረከባል። የሰራውም ወንጀል የወንጀል ሕግ ቁ 692ን ይጥሳል።ወንጀሉ ሁለት ክፍሎች ያሉት ሲሆን ኣንደኛው የሐሰት ደብዳቤ መፃፉ ሁለተኛው ደግም ግመሉን በዚሁ በማጭበርበሪያ ደብዳቤ መሰረት መረከቡ ናቸው። ደብዳቤው የተፃፈው በምስራቅ ሸዋ ዞን ስለሆነ ክሱ በምስራቅ ሸዋ ወይም በምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊሰማ ይቻላል።
- በሌላ ምሳሌ ተከሳሹ ያለኣግባብ ኣንዱን ሰው በኣላማጣ ወረዳ ቢይዘውና መሆኒ ወረዳ ወደ ሚገኘው ፓሊስ ጣቢያ ቢወስደው የወንጀል ሕግ ቁ 584ን የመጣስ ወንጀል ስለሚሆንና ይህ ሰውየውን ከሕግ ዉጪ በግድ የመያዙ የወንጀል ስራ ያለማቋረጥ ስለቀጠለ ክሱ በኣላማጣ ወይም በመሆኒ ወረዳ ፍርድ ቤት ሊታይ ይችላል።

# አካባቢያዊ ሥልጣን

- ይህ ዓይነት ስልጣን ነገሩ በክልል ፍርድቤት የሚዳኝ ከሆነ የት ክልል ወይም በአንድ ክልል ዉስጥ የቱ የወረዳ ወይም ዞን ፍርድ ቤት ነው ጉዳዩን አይቶ የመወሰን ስልጣን ያለው የሚለውን የምንወስንበት ነው። የወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ 6 እንደሚያመላክተው በተለያዩ ኣከባቢ የሚገኙ ፍርድ ቤቶች በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ 99-107 የተወሰነላቸውን ቦታ መሰረት ኣድርገው የዳኝነት ተግባራቸውን የማከናወን ስልጣን አላቸው። ማንኛውም የወንጀል ክስ **ወንጀሉ በተፈፀመበት ኣካባቢ በሚገኘው የሥረነገር** ስልጣን ባለው ፍ/ቤት ቀርቦ እንደሚታይ የወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ 99 ይደነግጋል።ለምሳሌ የወንጀሉ ዓይነት በወረዳ ወይም በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሚታይ ሊሆን ይችላል። ይህ የወረዳ ፍርድቤት የትም የሚገኝ ወረዳ ፍርድቤት ሳይሆን ነገሩ የተከሰተበት ወረዳ ዉስጥ የሚገኝ የወረዳ ፍርድቤት ብቻ ነዉ።
- በሌላ በኩል ደግሞ ወንጀሉ የተፈፀመበትና የወንጀሉ ወጤት የታየበት ኣከባቢ የተለያየ የሚሆንበት ኣጋጣሚ ሊኖር ይችላል። ይህም ማለት ወንጀሉ የተፈፀመው በኣንድ ወረዳ ወይም ዞን ሲሆን የወንጀሉ ውጤት የታየበት ደግሞ በሌላ ወረዳ ወይም ዞን ሊሆን ይችላል። በዚህ ጊዜ ሁለቱ ፍ/ቤቶች ማለትም ወንጀሉ በተፈፀመበት ኣከባቢ የሚገኝ የወረዳ ወይም የዞን (ከፍተኛ) ፍ/ቤት ወይም የወንጀሉ ውጤት በታየበት ኣካባቢ የሚገኝ የወረዳ /ዞን (ከፍተኛ) ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ አካባቢያዊ ስልጣን ኣላቸው ማለት ነው።

# አካባቢያዊ ሥልጣን

- በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 103 መሰረት ወንጀሉ የተፈፀመው ተጠርጣሪው በጉዞ ላይ ሳለ ቢሆን ተጠርጣሪው ወይም ወንጀሉ የተፈፀመበት ሰው ወይም ነገር በጉዞው በሚያልፍበት ስፍራ ውስጥ ክሱን ለመስማት የሥረነገር ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ክሱ ይታያል። ተጠርጣሪው ወንጀል የፈፀመበት ሰው ወይም ሌላ ነገር (ንብረት) በስፍራው ካለፈ ወንጀሉ በዛው ስፍራ ባይፈፀምም ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት በነገሩ ሊፈርድ ይችላል። ኣንድ ወንጀል ከኢትዮጵያ ግዛት ውጭ በኢትዮጵያ መርከብ ላይ ወይም ኤሮፕላን ውስጥ ቢፈፀም ኢትዮጵያ ውስጥ እንደተፈፀመ ይቆጠራል (የወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ ቁ.104)። ይህ ቁጥር ክሱ በየትኛው የኢትዮጵያ ፍርድ ቤት መታየት እንደሚገባው ኣይገልፅም።
- ከአካባቢያዊ ስልጣን ጋር ተያይዞ መታየት ያለበት ሌላ ነገር ኣንድ ክስ ካንድ ነገሩን ለማየት ስልጣን ካለው ፍርድ ቤት ወደ ሌላው ፍርድ ቤት የመዛወሩ ጉዳይ ነው። የሚመለከተው ፍርድ ቤት ኣንድ ክስ ከአንድ ፍርድ ቤት ወደ ሌላ ለማስተላለፍ የቀረበለትን ማመልከቻ የሚቀበልበት ኣራት ሁኔታዎች እንዳሉ ቁጥር 106 ያመለክታል። እነዚህም የሚከተሉት ናቸው። ሀ) የበታች ፍርድ ቤት በልዩ ልዩ ምክንያቶች ኣድልዎ የሌለበት ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት እንደማይችል ግልፅ ሲሆን ፣ ለ) ክሱ በጣም ኣስቸጋሪና ከባድ የሆነ ለውሳኔ የሚያዳግት የሕግ ጉዳይ ሲኖርበት ፣ ሐ) የክሱ መዛወር ለባለጉዳዮችና ለምስክሮች በቦታው ቅርበትም ሆነ በሌላ ምክንያት ምቹ ወይም ተፈላጊ ሲሆን ፣ እና መ) በአጭር ጊዜ ትክክለኛ ፍርድ የሚገኘው በክሱ መዛወር ብቻ ሲሆን ወይም የክሱ መዛወር በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ- ስርዓት የተፈቀደ ሲሆን ነው።
- ምሳሌ 1 እና ምሳሌ 2 ለውይይት የሚቀርብ ነው (ገጽ 92)

# ርዕሶች

- ክስ ስለመስማት፣ ክስ ለመስማት የሚደረጉ ዝግጅቶች ፣ ቀን መቁረጥና ተከራካሪዎችን ከነምክሮቻቸው ስለመጥራት
- ክስን  ለተከሳሽ ስለማድረስ
- በቀጠሮ አለመገኘትና ውጤቱ፥
- ተከሳሽ ባለመቅረቡ የሚወሰድ ርምጃ፣  ዐቃቤ ህግ ባለመቅረቡ የሚወሰድ ርምጃ፣ ምስክር ባለመቅረቡ የሚወሰድ ርምጃ
- ተከሳሽ ሲቀርብ የሚፈጸም ሂደት ፤ ክስ ስለመስማት፣ ነገሩን በግልጽ ችሎት ስለማየት፣ በጠበቃ ስለመከራከር፣ በአስተርጉዋሚ ስለመታገዝ
- ክስን ስለመቃወምና በመቃወሚያው ላይ ስለመወሰን፣ ክስን ማሻሻል እና ክስ ማንሳት
- ዕምነት ክህደት ስለመስጠት፥ ዕምነት ቃል፣ ስለክህደት ቃል፣ ስለዕምነት ክህደት መለወጥ
- ስለማስረጃ አቀራረብ ና ስለቀጠሮ፣ ምስክሮች ሳይቀርቡ ወይም ሳይሙዋሉ ሲቀሩ የሚፈጸም ሥ/ሥ

ርዕሶች፡-

- ክስ ስለመስማት፣ ክስ ለመስማት የሚደረጉ ዝግጅቶች ፣ ቀን መቁረጥና ተከራካሪዎችን ከነምክሮቻቸው ስለመጥራት
- ክስን ለተከሳሽ ስለማድረስ
- በቀጠሮ አለመገኘትና ውጤቱ፡
- ተከሳሽ ባለመቅረቡ የሚወሰድ ርምጃ፣ ዐቃቤ ህግ ባለመቅረቡ የሚወሰድ ርምጃ፣ ምስክር ባለመቅረቡ የሚወሰድ ርምጃ
- ተከሳሽ ሲቀርብ የሚፈጸም ሂደት ፡ ክስ ስለመስማት፣ ነገሩን በግልጽ ችሎት ስለማየት፣ በጠበቃ ስለመከራከር፣ በአስተርጉዋሚ ስለመታገዝ
- ክስን ስለመቃወምና በመቃወሚያው ላይ ስለመወሰን፣ ክስን ማሻሻል እና ክስ ማንሳት
- ዕምነት ክህደት ስለመስጠት፡ ዕምነት ቃል፣ ስለክህደት ቃል፣ ስለዕምነት ክህደት መለወጥ
- ስለማስረጃ አቀራረብ ና ስለቀጠሮ፣ ምስክሮች ሳይቀርቡ ወይም ሳይሙዋሉ ሲቀሩ የሚፈጸም ሥ/ሥ

- ክስን ስለመቃወምና በመቃወሚያው ላይ ስለመወሰን
- ክስን ማሻሻል እና ማንሳት
- ክስ ማንሳት
- ዕምነት ክህደት ስለመስጠት፣
- ዕምነት ቃል
- ስለክህደት ቃል
- ስለዕምነት ክህደት መለወጥ
- ስለማስረጃ አቀራረብ ና ስለቀጠሮ
- ምስክሮች ሳይቀርቡ ወይም ሳይሙዋሉ ሲቀሩ የሚፈጸም ሥ/ሥ

- ምስክሮች ስለመስማት ፤
- የዐ/ህግ ማስረጃ አሰማም ና በማስረጃ ላይ የሚሰጥ ውሳኔ፡
- የዐ/ህግ ምስክር መስማት
- የዐ/ህግ ማስረጃ እንደ ክሱ ባላስረዳ ጊዜ የሚፈጸም ሥ/ሥ
- የዐ/ህግ ምስክሮች እንደ ክሱ ባስረዱ ጊዜ የሚፈጸም ሥ/ሥ
- ስለመከላከያ ማስረጃ ፤
- የመከላከያ ምስክሮችን መስማት
- በማስረጃ መስማት ጊዜ የፍ/ቤት ሚና
- ዳኞች ተጨማሪ ምስክር እንዲቀርብ ለማዘዝ ይችላሉ
- የክርክር ማቆሚያ ንግግር/የመፋረጃ ሃሳብ/
- ስለፍርድ አሰጣጥና አጻጻፍ
- የቅጣት አወሳሰን

ክስ መስማት

- ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ያለው መሆኑን ሲያረጋግጥ ክሱን ተቀብሎ ወደ ክስ መስማት ሂደት ያመራል፡፡ ይህ ሂደት ተከሳሾችን አጥፊ ነው ወይም ንጹህ ነው ብሎ ለመደምደም የግራ ቀኙን ምስክሮችን መስማትና የግራኙን ክርክር በጥንቃቄ መምራት ይጠይቃል፡፡ክርክሩን ለማስፈጸም የወ/ሥ/ሥ/ህጉን ድንጋጌዎች መከተል ያስፈልጋል፡፡ የሥ/ሥ/ህግ ድንጋጌዎችን የግራ ቀኙን መብቶች ና ጥቅሞች ለማመዛዘን ወይም ለማቻቻል በሚያስችል ሁኔታ የተደነገጉ ስለሆነ ተፈጻሚ ለማድረግ ከባለሙያዎች ብዙ ይጠበቃል፡፡
- **ክስ ለመስማት የሚደረጉ ዝግጅቶች ፤**
- **ቀን መቁረጥና ተከራካሪዎችን ከነምክሮቻቸው ስለመጥራት(127)**
- ክስን  ለተከሳሽ ስለማድረስ
- በቀጠሮ አለመገኘትና ውጤቱ፡

- ፍርድቤቱ ክስ ከቀረበለት በኋላ ነገሩን ለማየት ሥልጣን ያለዉ ከሆነ ክሱን የሚሰማበትን ቀን በመወሰን ለመዝገቡ ቀጠሮ ይሰጠዋል። በዚህ ቀን ተከሳሽ ክሱን ለመከላከል እንዲችል መቅረብ ስላለበት /የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ/ 127/ እንዲቀርብና መልስ እንዲሰጥ መጥሪያ ይላክለታል። ከዚህ መጥሪ ጋር ተያይዞም የክሱ ቅጂ ከነሰነድ ማስረጃዉ ይላክለታል። ዓቃቤ ሕጉም ክሱን ለመስማት በተቀጠረበት ቀን እንዲቀርብ መጥሪያ ይላክለታል። ክሱ የሚሰማበት ቀን ለመወሰን ሌላ ቀጠሮ ሳያስፈልገው ፋይሉ እንደተከፈተና ፍርድቤቱ ሥልጣን እንዳለዉ እንዳረጋገጠ ወድያው ቀነ ቀጠሮ ተለይቶ ሊቀመጥ ይገባል። ፍርድ ቤቱ ክሱ የሚሰማበትን ቀን ሲወስን እንዲሁ በግምት ሳይሆን ተከሳሹ የሚገኝበት ቦታ ቅርበትና ርቀት፤ ምስክሮች የሚገኙበትና ለመቅረብ የሚወስድባቸው ጊዜ፤ የፍርድ ቤቱ የመዝገብ ብዛት ወዘተ ግምት ውስጥ በማስገባት መሆን አለበት። የቀጠሮ ቀን ስለመወሰንና ስለመጥሪያ አላላክ የወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ.123 ይመለከቷል።
- ልዩ ሁኔታ የሚኖረው በ RTD አሰራር የሚታዩ ጉዳዮች ላይ ነው። ተከሳሽ ና ምስክሮች አብረው ችሎት ይቀርቡና ይሰማሉ፣ ምናልባት ቀጠሮ የሚሰጠው ተከሳሽ እንዲከላከል ተበይኖ መከላከያ አቀርባለሁ ሲል ነው።የRTD አሰራር መሰረታዊ መብቶችን(በጠበቃ መከራከር፣መከላከያ ማቅረብና አስፈላጊ የሆኑ ክርክሮችን መቃወምያን ጨምሮ ለማቅረብ እንደማያግድ መረዳት ያስፈልጋል።(ቅጽ 17፣ መ.ቁ.100712 ገጽ 213)

- ክሱ የሚሰማበት ቀን እንደተወሰነ ሌላ መደረግ ያለበት **ዓ/ሕጉና ተከሳሹ የምስክሮቻቸውን ዝርዝር ለፍርድ ቤቱ ሬጂስትራር ማቅረብ ነው (የወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ.124)**። የማስረጃው ዓይነት የክሱ ፍሬ ነገር በቀጥታ ሆነ ቀጥታ ባልሆነ መንገድ የሚያውቁ ምስክሮች እና/ ወይም ልዩ እውቀት ያላቸው ሰዎች (ኤክስፐርቶች) ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚህ ምስክሮች ነገሩ በሚሰማበት ቀን ቀርበው የምስክርነት ቃላቸውን መስጠት እንዲችሉ በፍርድ ቤቱ ሬጂስትራር በኩል መጥሪያ ይላክላቸዋል። የተለመደዉ አሰራር ክሱ የሚሰማበት ቀን ሲቆረጥ ዐቃቤህግና ተከሳሽ እንዲቀርቡ መጥሪያ መላክ የነበረ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ደግሞ በአንዳንድ ፍርድቤቶች ግራ ቀኙ ምስክሮቻቸዉን ይዘዉ እንዲቀርቡ ይታዘዛል። ነገር ግን እነዚህ ተፈላጊ ሰዎች ተሟልተዉ ላይቀርቡ ስለሚችሉ ምስክሮች ቀርበዉ ተከሳሽ ባይቀርብ ምስክሮች ሊጉላሉ ነዉ። **የተከሳሽ ምስክሮች ቀርበዉ የዐቃቤህግ ምስክሮች ባይቀርቡ ዐቃቤህግ ማስረጃዉን ሳያቀርብ ተከሳሽ ሊያቀርብ ስለማይገባ የተከሳሽ ምስክሮች አላግባብ ሊደክሙ ነዉ።** ስለዚህ ክሱ የሚሰማበት ቀን ከተቆረጠ በኋላ ስለተፈላጊሰዎች አቀራረብ የሚሰጠዉ ትዕዛዝ ለዚህ ችግር መፍትሄ የሚሰጥ ሊሆን ይገባል።

## ክስን ለተከሳሽ ስለማድረስ(ህ/መት 20/2/+ሥ/ሥ/ህ/ቁ.109/4/+94/2/ሰ/)

- ፍርድ ቤት የቀረበለትን ክስ ለማየት ስልጣን ያለው መሆኑን ያረጋገጠ እንደሆነ የክሱ ግልባጭ ክሱ ከሚሰማበት ቀን በእጅጉ ቀደም ብሎ እንዲደርሰዉ ለተከሳሹ ሊልክለት እንደሚገባም **የወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ.109 (4) እና 94/2/ሰ/ ይደነግጋሉ፡፡** ይህ የክስ ግልባጭ የማግኘት መብት በኤፌዴሪ ሕገ መንግስት እውቅና ኣግኝቷል፡፡ ይህ ድንጋጌ **በሕገ መንግስቱ ዓንቀፅ 20 (2) የተመለከተ ሲ**ሆን፤ የተከሰሱ ሰዎች ክሱ በቂ በሆነ ዝርዝር እንዲነገራቸው እና ክሱን በፅሑፍ የማግኘት መብት እንዳኣላቸው በግልፅ ሁኔታ ተቀምጧል፡፡ ከሕገ መንግስቱ ድንጋጌ መረዳት እንደሚቻለው የተከሰሱ ሰዎች የክሱ ግልባጭ (በፅሑፍ) ሊደርሳቸው ይገባል ብቻ ሳይሆን የክሱ ማመልከቻ በበቂ ሁኔታ ዝርዝር ነገሮችን መያዝ እንዳለበትና ተከሳሾች የተከሰሱበት ጉዳይ በሚገባ እንዲረዱ የሚያስችላቸው መሆን እንደአለበት ነው፡፡ ክስ ከማድረስ ጋር ተያይዞ ሊነሳ የሚገባዉ ተግባር **ማስረጃን የማግኘትና የማየት መብትን የሚመለከት ነዉ፡፡ በተለይም ይህ ማስረጃን የማየት ወይም የማግኘት መብት ተፈጻሚ የሚሆነዉ መቼ ነዉ የሚለዉ ጭብጥ ትኩረት የሚሻ ነዉ፡፡**
- ለተከሳሽ የክስ ማመልከቻዉ ቅጂ ከቀጠሮዉ ቀን እጅግ ቀደም ብሎ እንዲደርሰዉ ሲላክለት ከምን ጋር አንደሚላክለት በሥነሥርዓት ህጉ የተደነገገ ነገር የለም፡፡ የዚህ አይነት ሥነሥርዓት ምናልባት በሙስና ወንጀሎች ሥነሥርዓት ህግ መሰረት የቅድመክስ ሂደት የሚከናወን ከሆነ ዐቃቤህግ መግለጫ ሲሰጥ አብሮ ማስረጃዎቹን አያይዞ እንዲሰጥ በሚደረግበት አጋጣሚ ጊዜ ሊያጋጥም ይችላል፡፡ ቀደም ሲል በነበረዉ የፍርድቤቶች አሰራር ልማድ መሰረት የክስ ቅጂ ለተከሳሽ የሚላከዉ ብቻዉን እንዲያዉም የማስረጃ ዝርዝር እንኳ የሌለዉ ቅጂ ነበር፡፡ የሰነድ ማስረጃ ካለ እንዲደርሰዉ ይደረግ የነበረዉ ተከሳሽ ቀርቦ ክሱ ተሰምቶ የዐቃቤህግ ምስክሮች ተሰምተዉ ሲያበቁ ነበር፡፡

# ክስን ለተከሳሽ ስለማድረስ

- ለተከሳሽ የክስ ማመልከቻዉ ቅጂ ከቀጠሮዉ ቀን እጅግ ቀደም ብሎ እንዲደርሰዉ ሲላክለት ከምን ጋር እንደሚላክለት በሥነሥርዓት ህጉ የተደነገገ ነገር የለም። የዚህ አይነት ሥነሥርዓት ምናልባት በሙስና ወንጀሎች ሥነሥርዓት ህግ መሰረት የቅድመክስ ሂደት የሚከናወን ከሆነ ዐቃቤህግ መግለጫ ሲሰጥ አብሮ ማስረጃዎቹን አያይዞ እንዲሰጥ በሚደረግበት አጋጣሚ ጊዜ ሊያጋጥም ይችላል። ቀደም ሲል በነበረዉ የፍርድቤቶች አሰራር ልማድ መሰረት የክስ ቅጂ ለተከሳሽ የሚላከዉ ብቻዉን እንዲያዉም የማስረጃ ዝርዝር እንኳ የሌለዉ ቅጂ ነበር። የሰነድ ማስረጃ ካለ እንዲደርሰዉ ይደረግ የነበረዉ ተከሳሽ ቀርቦ ክሱ ተሰምቶ የዐቃቤህግ ምስክሮች ተሰምተዉ ሲያበቁ ነበር።
- ስለሰነድ ማስረጃዎች አቀራረብ ግልጽ የሆነ ድንጋጌ ባለመኖሩ ከላይ የተገለጸዉ አሰራር ተስፋፍቶ የነበረ ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ ዐቃቤህግ ከክስ ማመልከቻዉ ጋር የሰነድ ማስረጃዎቹን ቅጂ አያይዞ እንዲያቀርብ እየተደረገ ይገኛል። ስለዚህ በአሰራር በዳበረዉ የአሁኑ ጊዜ ልማድ ተከሳሽ ከክስ ማመልከቻዉ ቅጂ ጋር የሰነድ ማስረጃዎች እንዲደርሰዉ ይደረጋል። የማስረጃው ግልባጭ ከክሱ ቅጂ ጋር ለተከሳሹ እንዲደርሰው ማድረግ ያለው ፋይዳ ተከሳሹ የተመሰረተበት ክስና ክሱን ለማስረዳት የቀረበበት ማስረጃ በቂ ጊዜ አግኝቶ እንዲያየውና እንዲመረምረው ያስችለዋል፤ ለክሱ የሚሰጠዉ መልስ ወይም የሚያቀርበዉ ክርክር በደፈናዉ ሳይሆን በተሟላ መረጃ ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ያደርጋል፣ የመከላከል ዓቅሙ እንዲጎለብት ያስችለዋል።

## በቀጠሮ አለመገኘትና ዉጤቱ ፡- ተከሳሽ ባለመቅረቡ የሚወሰድ ርምጃ

- ከፍ/ቤት የተላከው መጥሪያ ባግባቡ ደርሶት ተከሳሽ በቀጠሮ ቀን ያልቀረበ እንደሆነ ፍ/ቤት ፖሊስ አስሮ እንዲያቀርበው ትዕዛዝ ይሰጣል፣ታስሮ ሲቀርብም ክሱ መሰማት ይቀጥላል(ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 125 +160/2/)
- በሌላ በኩል ተከሳሽ መጥሪያ የተላከለት ቢሆንም **ተፈልጎ ሊገኝ ባለመቻሉ መጥሪያዉ ሳይደርሰዉ ይቀራል፡፡** በዚህም ጊዜ ፖሊስ ተከሳሹን አለማግኘቱን በመግለጽ በተለዋጩ ቀጠሮ እንዳቀርበዉ ተለዋጭ ቀጠሮ ይሰጠኝ የሚል መልስ ወይም ተከሳሹ ሊገኝ ስለማይችል ማቅረብ እንደማይችል በመግለጽ መልስ ይሰጣል፡፡ በዚህ ጊዜ ፍርድቤት እና ዐቃቤህግ ምን ሊያደርጉ ይገባል የሚለዉ አከራካሪ እየሆነ ይገኛል፡፡ ሌላዉ ጥያቄ ፖሊስ ተከሳሽን ይዞ እንዲያቀርብ የተሰጠው ትእዛዝ አፈጻጸም ሳይሳካለት ቢቀርስ (ለመያዝ ፈልጎ ቢያጣውስ) የሚወሰድ እርምጃ ምንድን ነው የሚል ይሆናል፡፡ ይህ ጥያቄ በሁለት መንገድ ሊመለስ የሚችል ነው፡፡ ይኸውም ተከሳሽ በቂ ባልሆነ ምክንያት ክስ እንዲሰማ በተቀጠረበት ቀን ያልቀረበ እንደሆነ ተከሳሹ በሌለበት ክሱ እንዲሰማ ፍ/ቤቱ ሊያዝዝ ይችላል (ቁ.160-163) ፡፡

## .........ተከሳሽ ባለመቅረቡ የሚወሰድ ርምጃ

- ይህ ዓይነት ትእዛዝ ሊሰጥ የሚቻለው ለሁሉም የወንጀል ዓይነቶች ሳይሆን በቁ.161 (2) እንደተመለከተው፤ **ከአስራ ሁለት ዓመት በማያንስ ፅኑ እስራት የሚያሳስር ወንጀል የሰራ ወይም በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ከቁ.354 እስከ 365 (በአዲሱ ወንጀል ሕግ ከቁ 343 እስከ 354) ድረስ ያሉትን ወንጀሎች ፈፅሞ ፅኑ እስራት ወይም ከአምስት ሺህ ብር በላይ መቀጫ በሚያስቀጣ ወንጀል የተከሰሰ ሲሆን ነው፡፡** በሌሎች የወንጀል ዓይነቶች የተከሰሱትን ተከሳሾች በሚመለከት ግን መጥሪያ ደርሶኣቸው ባይቀርቡም እንኳ በተገኙበት ጊዜ የክሱ መሰማት ሂደት እንዲቀጥል ለማድረግ መዝገቡ ተዘግቶ እንዲቆይ ከማዘዝ በስተቀር ተከሳሾቹ በሌሉበት ክሱ ሊሰማ አይችልም፡፡
- ተከሳሽ ከፍርድቤት የሚቀረዉ በመጀመሪያዉ ጥሪ ጊዜ ብቻ አይደለም። ተከሳሽ ከተጠራ በኋላ መቅረብ ጀምሮ ሊቀር ይችላል። የዐቃቤህግ ማስረጃዎች ከመሰማታቸዉ በፊት እንዲህ ያለዉ መቅረት ክሱ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 161/2/ የተመከቱትን ወንጀሎች የተመረኮዘ እስከሆነ ድረስ ተከሳሹ በሌለበት ይታያል። እንዲህ አይነት ወንጀሎችን የሚመለከት ክስ ከሌለ ግን ክሱ ሊቋረጥ ይገባል። በሌላ አጋጣሚ ተከሳሽ የዐቃቤህግ ምስክሮች ከተሰሙ በኋላ ፍርድቤቱ በነገሩ ላይ ብይን ለመስጠት ቀጠሮ ከያዘበት ቀን አንስቶ ከዚህ በኋላ በሚኖሩ ቀጠሮዎች ከፍርድቤት ሊቀር ይችላል። (ቅጽ 13 መ.ቁ. 76909 ገጽ 305-307)

# ዐቃቤ ህግ ባለመቅረቡ የሚወሰድ ርምጃ

- ክሱ ሊሰማ በተቀጠረበት ቀን ዐቃቤህግ ሳይቀርብ ቢቀር ምን ሊደረግ እንደሚገባዉ በሚነሳዉ ጥያቄ ላይ የሚሰጡት መፍትሄዎች ከቦታ ቦታ ከባለሙያ ባለሙያ ይለያያሉ፡፡ አንዳንድ ቦታ በአንዳንድ ዳኞች የሚሰጠዉ መፍትሄ መዝገቡን መዝጋት ነዉ፡፡ ሌሎች ደግሞ ዐቃቤህግ ሲቀርብ ክሱን መስማት ለመቀጠል ቀጠሮ ይለዉጣሉ፡፡ የመጀመሪያዉ መፍትሄ ከተከሳሹ በተገቢዉ ፍጥነት ፍርድ የማግኘት መብት አኳያ መዝገቡ የሚዘጋበት ምክንያት ሳይገለጽ ለነገሩ መቋጫ ሳይደረግ ማለትም በጉዳዩ ላይ ሳይወሰን መዝገቡን መዝጋት ይህን የተከሳሹን መብት አንጠልጥሎ የሚተዉ ነዉ፡፡ በህግ የሚደገፍ መሆኑም ያጠራጥራል፡፡ ወደሁለተኛዉ መፍትሄ ስንመጣ በተመሳሳይ ሁኔታ የተከሳሹን መብት የሚጎዳ ሆኖ ይገኛል፡፡ ይህን በፍጥነት ፍርድ የማግኘት መብት ለመንከባከብ ሲባል የተደነገገዉን የቀጠሮ ድንጋጌ /የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 94/2//ሀ/ ስር የተደነገገዉን የሚያፈርስ ነዉ፡፡ በዐቃቤህግ አለመቅረብ ምክንያት ቀጠሮ ሊለወጥ የሚችለዉ በምን ሁኔታ እንደሆነ ተደንግጎ ስለሚገኝ ሁልጊዜ ዐቃቤህግ እንዲቀርብ ለመጠበቅ ቀጠሮ መለወጥ ይህን ድንጋጌ ያልተከተለ አሰራር ይሆናል፡፡
- በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 94/2//ሀ/ መሰረት ዐቃቤህግ ሲቀር በዚህ ዕለት ቀጠሮ ለመለወጥ ከቀጠሮ የቀረዉ በበቂ ምክንያት መሆኑ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ ይህም ቀጠሮ ከመለወጡ በፊት መከናወን አለበት፡፡ ይህን ምክንያት ለማጣራት ቀጠሮ መለወጥ ይህን የቀጠሮ ድንጋጌ የሚከተል አይሆንም፡፡ በቂ ምክንያት መኖሩ በዚሁ ቀን ለፍርድቤት ቀርቦ መረጋገጥ አለበት፡፡

# ምስክር ባለመቅረቡ የሚወሰድ ርምጃ

- እንደተከራካሪዎቹ ሁሉ ምስክሮችም የማይቀርቡበት አጋጣሚ አለ። ልክ እንደተከሳሹ ሁሉ ምስክርም በሁለት ሁኔታዎች ሳይቀርብ ሊቀር ይችላል። አንድኛዉ ሳይገኝ በመቅረቱ መጥሪያ ስላልደረሰዉ ማለትም መጠራቱን ባለማወቁ ሲሆን ሌላኛዉ ከተጠራ በኋላ ለመቅረብ ባለመፈለጉ ወይም ቢፈልግም ከአቅም በላይ የሆነ እክል ስላጋጠመዉ ሊሆን ይችላል።
- በምስክር አለመቅረብ ምክንያት በፍርድቤቶች የሚወሰደዉ የተለመደዉ ርምጃ በቅድሚያ ቀጠሮ መለወጥ፣ ከበርካታ ወይም ከመጠነኛ ተደጋጋሚ የቀጠሮ ለዉጥ በኋላ ምስክር አሁንም ሊቀርብ ካልቻለ የተለመደዉ አሰራር የክሱን መሰማት ምስክር እስኪገኝ አቋርጦ መቆየት ወይም ምስክሩ በምርመራ ጊዜ የሰጠዉ ነዉ የተባለዉን ቃል በጽሁፍ የተቀመጠዉን በማስረጃነት እንዲቀር ማድረግ ነዉ።
- በርግጥም ምስክር ባልቀረበ ጊዜ ይኸዉ ቀጠሮ ለመለወጥ ምክንያት እንደሆነ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ/ 94/2//ለ/ ስር ተደንግጓል። ሆኖም ይህ ቀጠሮ የመለወጥ ነገር ከላይ በታዩት ሁሉም ምስክር የሚቀርባቸዉ ሁኔታዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆን እንደሁ መወሰን ያስፈልጋል። እንደሚታየዉ ድንጋጌዉ ሁኔታዎቹን በመለየት የሚደነግግ አይደለም። ሆኖም በምስክር አለመቅረብ ምክንያት ቀጠሮ ሲለወጥ ሊሰጡ የሚገባቸዉን ትዕዛዞች በተመለከተ የተደነገገዉን የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ/ 96 ከግንዛቤ በማስገባት ነገሩን መወሰን ያስፈልጋል። ይህ ድንጋጌ በዚህ ጊዜ እንዲሰጡ የሚደነግጋቸዉ ትዕዛዞች ቀጠሮ ሊለወጥ የሚችልባቸዉን ምክንያቶች ባህሪ የሚጠቁሙ ናቸዉ።

# ምስክር ባለመቅረቡ የሚወሰድ ርምጃ

- መጠራታቸዉን አዉቀዉ ያልቀረቡ ሰዎች በእስር እንዲቀርቡ ፓሊስን ማዘዝ ብቻ ሳይሆን ለፍትህ እርዳታ የመስጠት ግዴታቸውን ባለመወጣቸው ወይም እንዲቀርቡ ትእዛዝ ደርሶኣቸው እያለ እምቢ በማለታቸው ምክንያት ሊቀጡ እንደሚችሉ በወንጀል ሕግ ዓንቀፅ 448 ተመልክቷል፡፡ ስለዚህ ይህ ህግ ተፈጻሚ እንዲሆን ማድረግ ለዚህም ከመጀመሪያዉ ጥሪ ጋር ይህን የቅጣት ማስጠንቀቂያ ጨምሮ ማዘዝ ተገቢ ይሆናል፡፡

## ተከሳሽ ሲቀርብ የሚፈጸም ሂደት

- አንድ ሰዉ በቀረበበት ክስ ምስክንያት ተጠርቶ ፍርድቤት ሲቀርብ ከክሱ ጋር በተያያዘ ሊደረግለት የሚገባዉ የመጀመሪያዉ ትልቅ ነገር የተከሰሰበትን ወንጀል በችሎት እንዲሰማዉና እንዲረዳዉ ማድረግ ነዉ። ሆኖም ይህ ከመሆኑ በፊት በዚህ ክስ የሚፈለገዉ ሰዉ እርሱ ስለመሆኑ ማጣራት ሊደረግ ይገባል። የተከሳሹን በሳጥን ውስጥ መግባት ተከትሎ መከናወን ያለበት ነገር ቢኖር የተከሳሹን ማንነት ማረጋገጥ ነው። በወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ቁ 128 እንደተመለከተው "ተከሳሹ በሳጥን ውስጥ ገብቶ ከቆመ በኋላ ማንነቱ፤ ዕድሜውና ስራዉ መረጋገጥ አለበት" ይላል። እዚህ ላይ ማንነት የሚል ቃል በሰፊው ካልተተረጎመ በስተቀር ስምን ብቻ ለማመልከት የተቀመጠ ነው የሚመስለው። ይሁን እንጂ ኣንድ ተከሳሽ ለፍ/ቤት መግለፅ ያለበት ስሙን፤ ዕድሜውና ስራውን ብቻ ሳይሆን፤ ፆታውን፤ ኣድራሻውን፤ የትምህርት ደረጃውንና የቤተሰቡን ሁኔታ (ያገባ ወይም ያላገባ መሆኑን፤ ልጆች ያሉት ወይም የሌሉት መሆኑን ወዘተ) ጭምር ነው። እነዚህ መረጃዎች ወደፊት ለሚሰጡ ዉሳኔዎች ጠቃሚ ናቸዉ።
- ተከሳሽ ሲቀርብ የሚፈጸም ሂደት ፡ <u>**ክስ ስለመስማት፣ ነገሩን በግልጽ ችሎት ስለማየት፣ በጠበቃ ስለመከራከር፣ በአስተርጉዋሚ ስለመታገዝ**</u>

## ነገሩን በግልጽ ችሎት ስለማየት፡-

- ክሱን ለመስማት በተቀጠረበት ቀንና ሰዓት ክሱን ለመስማት ፍርድ ቤቱ ማስቻል አለበት። የተከሳሹን ወይም የተበዳዩን የግል ህይወትና ሞራል፤ የህዝቡን የሞራልና የፀጥታ ሁኔታ እንዲሁም የአገሪቱን ደህንነት ለመጠበቅ ሲል ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን በዝግ ችሎት እንዲታይ ካልወሰነ በቀር ክሱ በግልፅ ችሎት መታየት ይኖርበታል (የኢፌዴሪ ሕገ መንግስት ቁ 20 (1) ።
- ይህም እንዲሆን ያስፈለገበት ምክንያት የአሰራረ ግልፅነት ግዴታ በመንግሥት የሥልጣን አካላት ላይ የተጣለ ስለሆነና ይህ ግዴታ መፈጸሙ ለፍትሕ ዋስትና በመሆኑ ነው። የግልፅ ችሎት አስፈላጊነት ለዳኛውም በራስ የመተማመን ሁኔታ ይፈጥርለታል። ፍትህ ፍለጋ ለሚመጣና ለኅብረተሰቡ በአጠቃላይ በፍትሕ ተቋሙ /ፍርድ ቤት/ ላይ ያለውን እምነት እየጠነከረ እንዲሄድ ያደርገዋል።

ነገሩን በግልጽ ችሎት ስለማየት፡-

- የክስ መሰማት ሂደት በግልፅ ችሎት እንዲካሄድ መደረጉ ችሎቱን የሚከታተሉ ወገኖች ዳኞች ገለልተኛነታቸውን ጠብቀው ባለጉዳዩችን በእኩልነት እያዩ ሂደቱን እየመሩ ስለመሆናቸው ለማረጋገጥ፤ የግራና ቀኝ ተከራካሪ ወገኖች ማስረጃና የሚሰጠውን ፍርድ ይዘት ለመገምገም ያስችላቸዋል። በአጠቃላይ ዳኞች ነፃነታቸውን ጠብቀው ሕግንና ህሊናቸውን መሰረት አድርገው ምን ያህል የዳኝነት ስራቸውን እያከናወኑ እንዳሉ ኅብረተሰብ እንዲገነዘብ ያስችለዋል። ፍርድ ቤቶች የህዝብ (የተገልጋይ) አመኔታ እንዲያተርፉ ከሚያደርጉዋቸው ነገሮች አንዱ ስራቸውን በግልፅ ችሎት ሲያካሂዱ ስለሆነ ያለው ፋይዳ ከፍተኛ ነው።
- ከተከሳሽ መብት አኳያ እንዲሁ ጠቀሜታዉ የሚናቅ አይደለም። ምክንያቱም ችሎቶች ግልጽ እና ባደባባይ መሆናቸዉ ተከሳሹ ያሉትን መብቶች በተገቢዉ መንገድ ሲገለገልባቸዉ ሊደርሱበት የሚችሉ መጋፋቶችን ያስቀራል። የታዛቢ የተመልካች መኖር ፍርድቤቶች ወይም ሌሎች ወገኖች ተከሳሹ መብቱን እንዳይሰራበት የሚያሰናክሉ ተግባራትን ከመፈጸም እንዲቆጠቡ ግፊት ስለሚያደርግ ከዚህ አኳያ የችሎት ሂደቶች ግልጽ መሆን ከፍተኛ አስተዋጽዖ አለዉ።

## በጠበቃ ስለመከራከር፡-

- ክስን የመስማት ጉዳይ ሲነሳ አብሮ የሚነሳው በጠበቃ የመታገዝ አስፈላጊነት ነው። የጠበቃ አስፈላጊነት በአጠቃላይ ሲታይ አንድ ተከሳሽ በሕግ የተቀመጠለት መብት በአግባቡና በተገቢ ሁኔታ እንዲጠቀምበት ለማስቻል ነው። ያለጠበቃ መከራከር የሚያስከትለው ጉዳት፡-
- የተማረ ሰው ቢሆንም እንኳ ሕግ የማያውቅ ከሆነ እራሱን ለመከላከል ያዳግተዋል፣

**. የክስ ይዘትና ፎርም ትክክል መሆኑንና አለመሆኑን ላያውቅ ስለሚችል በተገቢው** ሰዓት ተገቢውን ተቃውሞ ለማቅረበ አይችልም፣

. የማሰረጃ አቀራረብ ደንቦችን ስለማያውቅ ታማኝነትና አግባብነት የሌላቸው የዓቃቤ ሕግ ማስረጃዎች ተቀባይነት እንዳይኖራቸው ለማድረግ ጥረት አያደርግም፣

**. ወንጀል የፈፀመ መሆኑ ቢረጋገጥ እንኳ በሕግ መሰረት ይቅርታ ሊያደርግለት ወይም** ቅጣቱ ሊቀልለት የሚገባ መሆኑን ለማስረዳት አይችልም።

- ስለዚህ እነዚህን ችግሮች ለመቀነስ ወይም ለማስወገድ ተከሳሹ ጠበቃ ያለው እንደሆነ ከጠበቃው ጋር የመቅረብ መብቱ የተጠበቀ ነው። በጠበቃ የመታገዝ ጉዳይ ተከሳሹ ዓቅም ካለው በራሱ ወጪ የመረጠውን ጠበቃ ማቆም የሚችል ሲሆን፤ ጠበቃ ለማቆም ዓቅም ያጣ እንደሆነ ግን ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ ያለ ጠበቃ ቢከራከር ፍትሕ ሊጓደልበት ይችላል የሚል እምነት ሲኖረው ከመንግስት ጠበቃ እንዲያገኝ ሊያዝዝ ይችላል።

## በጠበቃ ስለመከራከር፡-

- ተከሳሹም ዓቅም ከሌለው ከመንግስት ጠበቃ የማግኘት መብት እንዳለው ከኢፌዴሪ ሕገ መንግስት ቁ 20(5) መረዳት ይቻላል፡፡ ተከሳሹ ጠበቃ እንደሌለው ገልፆ መንግስት እንዲመድብለት ከጠየቀ ጉዳዩን የያዘዉ ፍርድ ቤት በበኩሉ በመንግስት ወጪ ጠበቃ ሊመድብለት የሚገባ መሆን አለመሆኑን መመርመር ኣለብን፡፡ በዚህ ረገድ በተለይም ያለጠበቃ መከራከር የፍትህ መጓደል ሊያስከትል የማይችልበት አጋጣሚ አለ ብሎ መከራከር ይቻላል ወይ የሚለዉ ጥያቄ መነሳቱ የማይታለፍ ነዉ፡፡
- ተከሳሹ ጠበቃ የተመደበለት እንደሆነ ከጠበቃው ጋር ተመካክሮ ለመቅረብ የሚያስችለው በቂ ጊዜ ሊሰጠው ይገባል፡፡ ከጠበቃው ጋር ለመመካከር ቀጠሮ እንዲሰጠው ከጠየቀም የጉዳዩ ክብደትና ውስብስብነት ግምት ውስጥ በማስገባት ክሱን ወድያው መቀጠል የተከሳሹን የመከላከል መብት የሚነካ መሆኑን ፍ/ቤቱ በሚገባ ካመነበት ቀጠሮ መስጠት ይችላል፡፡ የተከሳሹን የመከላከል መብት የማይነካ ከሆነ ግን ሌላ ቀጠሮ መስጠት ሳያስፈልግ ለመመካከር የሚበቃ የተወሰነ ጊዜ ብቻ መስጠት በቂ ሊሆን ይችላል፡፡

## በአስተርጓሚ ስለመታገዝ፡-

- የክስ መስማት ሂደት ሲጀመር ሌላ ትኩረት የሚሻ ነጥብ ኣስተርጓሚ የመመደብ ጉዳይ ነው። ችሎቱ የሚካሄደው ተከሳሹ በማያዉቀው ቋንቋ ከሆነ ፍ/ቤቱ በመንግስት ወጪ ኣስተርጓሚ ሊመድብለት ይገባል (ሕገ መንግስት ዓንቀፅ 20 (7) እና የወ/መ/ሕ/ስ/ስ/ ቁ.126 (2) ይመለከቷል)። ኣስተርጓሚ የሚመደበው ተከሳሹ ሲያመለክት ወይም ተከሳሹ ባያመለክትም የችሎቱን ቋንቋ የማይገባው መሆኑን ፍ/ቤቱ ሲረዳው ነው። ቋሚ የፍ/ቤት ኣስተርጓሚዎች ካሉ የተከሳሹን ቋንቋ የሚረዳ ኣስተርጓሚ ፍ/ቤቱ ይመድባል። ቋሚ ኣስተርጓሚ ከሌለ ወይም ያሉት ኣስተርጓሚዎች የተከሳሹን ቋንቋ የማይረዱ ከሆነ ፍ/ቤቶች ለተከሳሹ ወይም ለዓ/ሕጉ (ለግል ተበዳዩም ጭምር) ዘመድ (የስጋ ወይም የጋብቻ) ያልሆነ ችሎታ ያለው ሌላ ሰው መርጠዉ ሲመደቡ ይስተዋላል። ሕጉ በግልፅ ያስቀመጠው ነገር ባይኖርም በተለምዶ ኣስተርጓሚው ክርክሩን መተርጎም ከመጀመሩ በፊት በእውነት ለማስተርጎም እንዲምል ይደረጋል። የመሃላ ቃሉም "በዚህ ፍ/ቤት የቀረበውን ክርክር በእውነትና የችሎታዬን ያህል ላስተረጉም እምላለሁ" የሚል መሆን አለበት። ምናልባት "እምላለሁ" ማለትን ሃይማኖቱ የማይፈቅድለት ከሆነ ሌላ ኣባባል እንዲጠቀም (ለምሳሌ "ኣረጋግጣለሁ" እንዲል) ሊፈቀድለት ይገባል።

# ክስን ስለመቃወምና በመቃወሚያዉ ላይ ስለመወሰን (130)

# የክስ መስማት ሂደት

# ልዩ ሥ/ሥርዓቶች

- የፀረ-ሙስና ሥ/ሥርዓት፣
- የዋስትና ሥ/ሥርዓት
- ዋስትና የሚከለከልበት ምክንያት
- የቅድመ ክስ ዝግጅት ሥ/ሥርዓት፣
- ዓላማውና የሚከናወንበት ምክንያቶች/በተግባር/
- የቅድመ ክስ ዝግጅትየሚደረግበትና የማይደግበት አጋጣሚዎች
- የማሰረጃ ልዩ ሥ/ሥርዓቶች
- የህግ ግምት ማስረጃ
- የግብረ አበር ምስክርነት
- የአስጠቂ ምስክር ሥ/ሥርዓት

# ስለወጣት አጥፊዎች ወንጀል ሥ/ሥርዓት

- የወጣት አጥፊነት ፍቺ
- በወጣት አጥፊዎች ጉዳይ የክስ አጀማመርና የምርመራ ሂደት
- የወጣት አጥፊዎች የፍርድ ሂደት
- በደንብ መተላለፍ የወንጀል ምርመራ- የተጠርጣሪ መያዝ አስፈላጊነት፣
- የተከሳሽ አቀራረብና የክስ መስማት
- የፍረድ አሰጣጥና የቅጣት አወሳሰን

# ተከሳሽ በሌለበት ክስ መስማት

- መርህ
- ቅድመ ሁኔታዎች
- የክሱ መሰማትና ፍርድ አሰጣጥ

# የወ/ል ተጠቂዎች መብቶች

- የወ/ል ተጠቂዎች በክስ ሂደት የመሳተፍ መብት

## ከፍርድ በሁዋላ የወ/ህ/ሥ/ሥ

- ስለይግባኝ ፤
- ስህተቶችን ማረም
- ቁጥጥር ማድረግ
- የይግባኝ መብትና ወሰኑ
- የይግባኝ መብት በፌደራልና በክልል ፍ/ቤቶች
- ስለትዕዛዝ ይግባኝና ተከሳሽ እንዲከላከል የሚሰጥ ብይን ላይ ይግባኝ ስለማለት

- ተከሳሽ በሌለበት የተሰጠ ፍርድ ና ይግባኝ
- በተከሳሽ ዕምነት መሰረት በተሰጠ የጥፋተኝነት ውሳኔ ላይ ይግባኝ ስለማለትና የዕምነት ቃልን ስለማሻሻል
- በቅጣት ውሳኔ ላይ ይግባኝ ስለማለት
- ስለይግባኝ ጊዜና ጊዜው ስላለፈ ይግባኝ
- የይግባኝ ክርክር ሂደትና የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሳኔ

# ስለቅጣት አፈጻጸም

- ቅጣት ከመፈጸሙ በፊት ስለሚገደብበትና ስለሚታገድበት ሁኔታ
- አወሳሰናቸው የሚገደቡ ቅጣቶች
- አፈጻጸማቸው የሚገደቡ ቅጣቶች
- አፈጻጸማቸው ለሌላ ጊዜ የሚተላለፍ/የሚታገድ/ቅጣቶች

# ልዩ ሥነሥርዓቶች

- እስካሁን ባየነዉ በመደበኛዉ ሥነሥርዓት ብቻ የሚመሩ ጉዳዮችን ሲሆን አንዳንድ ጉዳዮች የተከሳሹን ወይም የወንጀሉን ባህሪ መሰረት በማድረግ፣ ወይም ለህግ አስፈጻሚዉ የህግ ማስፈጸም አመቺነት ሲባል ወዘተ. የተለዩ ሥነሥርዓቶች በህግ እንዲታወቁ ተደርጓል። ስለዚህ ባለሙያዎች የዚህ አይነት ሥነሥርዓት የሚገዛቸዉን ጉዳዮች የሚያስተናግዱበት አጋጣሚ ስለሚኖር እነዚህን ሥነሥርዓቶች ማወቅና በነዚህ ሥነሥርዓቶች መስራትን መለማመድ ያስፈልጋቸዋል።

# 1. የጸረሙስና ሥነሥርዓት

- የወንጀል ምርመራ፣ ክስ አመራር፣አካሄድና ዋስትናን በሚመለከት በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርአት መጽሐፍ ከተመለከተው ውጭ አንዳንድ በባሕሪያቸውና አፈፃፀማቸው ለየት ይላሉ የሚባሉ ወንጀሎችን የምርመራ የማስረጃ አሰባሰበና ክስ አቀራረብን የሚደነግጉ የሥነ ሥርአት ድንግጌዎች አሉ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ አንዱ በአዋጅ ቁጥር 434/1997 የወጣው የፀረ ሙስና ልዩ የሥነ ሥርአትና የማስረጃ ሕግ ነው፡፡
- በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 7 ላይ የሙስና ወንጀሎችን ለማየት ሥልጣን የተሰጣቸው የፌዴራል ጠቅላይና ከፍተኛ ፍ/ቤቶች ሲሆኑ በክልሎች ደግሞ የክልል ጠቅላይና ከፍተኛ ፍ/ቤቶች ናቸው እንዲሁም ከሙስና ወንጀል ጋር በተያየዘ የሚነሱ የመያዝ፣ የብርበራ፣ የቀነ ቀጠሮ፣ በማረፊያ ቤት የማቆየት፣ የዋስትና የእግድ እንዲሁም ከምርመራ ጋር የተያያዙ ሌሎች ተመሣሣይ ጉዳዮች የሚታዩትም በእነዚሁ ከላይ በተጠቀሱት ፍ/ቤቶች መሆኑ በዚሁ አንቀጽ 7/4/ ላይ ተመልክቷል፡፡ ይህን ህግ በተመለከተ የተለዩ የሆኑ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ነጥቦችን ብቻ እናነሳለን፡፡

## የዋስትና ሥነሥርዓት ፡- ዋስትና የሚከለከልበት ምክንያት

- 434/97( አ/ጽ 4) + 882/2007(አ/ጽ 3/1) ዋስትና መጠየቅና መለቀቅ መብት ቢሆን በቅጣት መጠን ሁኔታ መነሻ በሙስና ወንጀል የተያዘ ሰው መብቱ ሊነፈግ ይችላል። ይህም የተከሰሰበት/የተጠረጠረበት ወ/ል ቅጣቱ 10 ዓመት በላይ ጽኑ እስራት የሚያስቀጣ ከሆነ፤ ከ4 ዓመት በላይ ከ10 ዓመት በታች የሚያስቀጡ ተደራራቢ ወ/ሎች ተደምረው 10 ዓመት በላይ የሚያስቀጡ ከሆነ ዋስትና ይከለከላል። ይህ ከመደበኛው ሥ/ሥርዓት ይለያል ።
- ዋስትና በፍ/ቤት ቢፈቀድ እንኳዋን ዐ/ህግ ይግባኝ እንደሚጠይቅ ለወሰነው ፍ/ቤት ካሳወቀ ተከሳሽ/ተጠርጣሪው አይለቀቅም(434/97 አ/ጽ 5/2/)፣ ይህ ከመደበኛው ሥ/ሥርዓት ይለያል።
- መርማሪ በዋስትና ማሰያዣ ወይም ወረቀት በማስፈረም በ ሥ/ሥ/ህ/ቁ 28 ዓይነት በአዋጁ አ/ጽ 4/2/ መሰረት ሊለቅ ይችላል። ሁኔታዎቹ በህጉ ላይ ተዘርዝረዋል

# የቅድመ ክስ ዝግጅት ሥ/ሥርዓት፤ ዓላማው

- <<የቀረበዉ ክስ ጭብጦችና የማስረጃዉ ዝርዝር ዉስብስብ በመሆኑ ምክንያት የፍርድ ሂደቱን የሚያራዝመዉና የሚያወሳስበዉ መስሎ ከታየዉና በዚህ አዋጅ አንቀጽ 36 የተመለከቱትን ዓላማዎች ሊያሟላ ይችላል በሎ ካመነ የቅድመክስ ዝግጅት እንዲከናወን ሊወስን...>> አ/ጽ 35
- ዓላማ+ ምክንያቶች(36) 1/ የቅድመክስ ዝግጅት ዓላማ የሚከተሉት ናቸዉ ሀ. ለክሱ አወሳሰን ሊረዱ የሚችሉ ጭብጦችን ለመለየት ለ. ባለጉዳዮች ጭብጦቹን እንዲረዱ እገዛ ለማድረግ ሐ. የክሱን ሂደት ለማፋጠን መ. ፍርድቤት የክሱን አካሄድ ለመምራት እንዲያስችለዉ ለማገዝ ነው። የፍ/ቤቱ ሥልጣን በ36/2/ላይ ተቀምጡዋል።
- የዚህ ዓይነት አካሄድ ጥቅሙ የጎላ ቢሆንም በተግባር ግን ይህ ሥ/ሥርዓት የቀረ ይመስላል።

## የማስረጃ ልዩ ሥነ-ሥርዓት፣ የግብረአበር ምስክርነት፣አስጠቂ ምስክር

- የህግ ግምት ማስረጃ ፡ አ/ጽ 57/2/ **<<ተቃራኒ ማስረጃ ካልቀረበ በቀር፣ የሙስና ወንጀሎቹ የተፈጸሙት የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም ለመጉዳት መሆኑ በተደነገገ ጊዜ በአንቀጹ ዉስጥ የተመለከተዉ ግዙፋዊ ፍሬ ነገር /ድርጊት/ እንደተፈጸመ ከተረጋገጠ፣ ድርጊቱ የተፈጸመዉ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለራስ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰዉ ለማስገኘት ወይም የሦስተኛ ወገንን መብት ወይም ጥቅም ለመጉዳት እንደሆነ ይገመታል።።>>** ይህ በመደበኛው ሥ/ሥርዓት ለማስረዳት አስቸጋሪ የሆኑ ሁኔታዎች ግም እንዲወሰድ ህጉ ለፍ/ቤት ፈቃድ ሰጠቱዋል፣የማስተባበል ግዴው ደግሞ የተከሳሽ ይሆናል ማለት ነው። መታለል ተገበሩ፣እምነት ማጉደሉ፣ስልጣን አላግባብ መገልገሉ ወዘተ ጥቅም ለማግኘት/ለማስገኘት እንደሆነ ይገመታል ማለት ነው፤ በዝህ ረገድ ዐ/ህግ ግገታውን ስለተወጣ ተከሳሽ ጥቅም ለማግኘት አለመሆኑን የመከላከል ሸክም ይኖርበታል
- **የግብረ አበር ምስክርነት እና ከክስ ነፃ ስለማድረግ** (43)፡ በዝርዝር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሲሆን ግለሰቡ ተከሳሽ ከሚሆን ምስክር ቢሆን ይሻላል የሚለው ሲታመንበት ነው። ይህ ለማድረግ በመደበኛው ሥ/ሥርዓት አልተከለከለም ግን ብዙ ጊዜ ጥቅም ላይ ሲውል አይታይም።
- **የአስጠቂ ምስክር ሥ/ሥርዓት(44)፡ ቀድሞ የሰጠው ምስክርነት vs. ፍ/ቤት የሚሰጠው ቃል። ምን ውጤት አለው ለሚለው 44(1-3) ተቀምጡዋል።**

## ስለወጣት አጥፊዎች ወንጀል ሥነሥርዓት

1. **ስለወጣት አጥፊዎች ፍቺ፡-** በአገራችን ህጻናት ዝቅተኛ የወንጀል ተጠያቂነት እድሜ በወ/ህ/ቁ 53 መሰረት 9 ዓመት ነው፡፡ ወጣት አጥፊዎች ተብለው የተለየ ጥበቃ የሚያገኙት እድሜያቸው **ከ9-15 ዓመት የሚሆኑ ህጻናት ናቸው፡፡** በዚህ ፅሑፍ ውስጥም ህጻናት ተብለው የሚጠቀሱትም እነዚሁ ክፍሎች ብቻ ናቸው፡፡ህጻኑ 15ኛ ዓመት ልደቱን ካከበረ ለወንጀል ህግ ጉዳይ እንደ አዋቂ ይቆጠራል፡፡ በወ/ህ/ቁ 56 መሰረት እድሜያቸው 15-18 ለሆኑት ህጻናት ጥበቃ የሚደረገው ከጥፋተኝነት ውሣኔ በኋላ በቅጣት ጊዜ ብቻ ነው፡፡የወጣት አጥፊነት ፍትህ ሂደትን የሚገዙት ድንጋጌዎች በወ/መ/ህ /ስ/ስ/ቁ 171-180 ያሉት ናቸው፡፡

2. **በወጣት አጥፊዎች ጉዳይ የክስ አጀማመርና የወንጀል ምርመራ ሂደት (172)**

**አካለመጠን ያላደረሰው ወጣት ወንጀል ሰርቶ በተገኘ ጊዜ ወላጅ ወይም ሚግዚት ፣ፖሊስ፣ዐ/ህግ፡፡ ፖሊስ ምርመራ ማድረግ የሚችልው ፍ/ቤት ሲፈቅለትና መመርያ ሲሰጠው ነው አለበለዚያ ምርመራ ማድረግ አይችልም፡፡**

3. **የወጣት አጥፊዎች የፍርድ ሂደት(176- 180)፡ ውሳኔው ጥፋተኛ ወይም ነጻ ነው ሊባል ይችላል፡፡ ጥፋተኛ ከተባለ ቅጣቱ ከመደበኛው የተየ ሲሆን ማስተካከያ እርምጃ እንጂ ቅጣት አይመስሉም(ወ/ል/ህ/ቁ 157-175)**

# ስለደንብ መተላለፍ (ሥ/ሥ. 167-170)

- በወ/ል/ህጉ አ/ጽ 734-865 የተመለከቱት በደንብ መተላለፍ የሚያስቀጡ ናቸው፡፡ ደንብ መተላለፍ ጉዳዮች የተለየ ሥ/ሥ በመከተል እልባት ይሰጥባቸዋል፡፡
- **ምርመራ እና የተርጣሪ መያዝ አስፈላጊነት፡** ከሚያስከትለው ቅጣት ዝቅተኛነት አንጻር ተከሳሽ ክሱ በሚሰማበት መቅረቡ አስፈላጊ ላይሆን ስለሚችል መልሱን በጽሁፍ(እምነት ወይም ክደት) ሊመልስ ይችላል(168) ፤ፍ/ቤቱ ተከሳሹ የግድ እንዲቀርብ የሚያዘው የሚጣልበት ቅጣት የማረፊያ ቤት እስር፤የግዴታ ስራ ወይም ማስጠንቀቂያ ወይም የመውቀስ ቅጣት ለመጣል ሲፈልግ ብቻ ነው፡፡(169(2) ከገንዘብ መቀጮ ውጭ ያሉት ቅጣቶች ካሉ ከመወሰናቸው በፊት ተከሳሹ እንዲከላከል እድል ሊሰጠው ይገባል፡፡ (169(2)
- ስለዚህ እንዲህ አይነቱን ወንጀል መነሻ በማድረግ ምርመራ ሲጣራ ተጠርጣሪዉን መያዝ ያስፈልግ እንደሆነ መወሰን ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ረገድ የመያዣ ትዕዛዝ አሰጣጥን የሚደነግጉት የወንጀለኛ መቅጫ ሥነሥርዓቱን ህጎች መመርመር እና ከዚህ ጋር ያለዉን ግንኙነት መወሰን ያሻል፡፡ /<<... ወንጀሉ የሚያስይዝ መሆኑ ...>> የሚለዉን ሃሳብ ያስታዉሷል/
- **የተከሳሽ አቀራረብና የክሱ መሰማት፡ 170**
- **የፍርድ አሰጣጥና ቅጣት ፡ 169**

# ተከሳሽ በሌለበት ክስ መስማት

- **መርህ፡** በወንጀል ተጠርጥሮ የተከሰሰ ሰው ፍርድ ቤት ቀርቦ ክሱ ደርሶትና ተረድቶት የመስማት ሕገ መንግሥታዊ መብት እንዳለው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንሥግሥት አንቀጽ 20 ደንግጓል፡፡ ይህ ማለት ግን የወንጀል ክስ ሁሉ ተከሳሽ ፍርድ ቤት ካልቀረበ ታይቶ አይወሰንም ማለት አይደለም፡፡ በሕግ ተለይተው በተመለከቱ ሁኔታዎችና ወንጀሎች ላይ ተከሳሽ በሌለበትም ክሱን ሰምቶ መወሰን ይቻላል፡፡
- በሌለበት ለመስማት ቅድመ ሁኔታዎች ተቀምጠዋል(160+161
- የክሱ መሰማትና ፍርድ አሰጣጥ ፡ እንደማኛውም ጉዳይ ተሰምቶ ይወሰናል(163)

## የወንጀል ተጠቂዎች መብቶች

### የወንጀል ተጠቂዎች በክስ ሂደት የመሳተፍ መብት፡-

- ተጠቂውን ከምርመራ እስከ ፍርድ ባለው ሂደት ውስጥ ሚና እንዲኖረው መፍቀድ ምክንያቱም ስለጉዳዩ ከሱ የተሻለ የሚያስረዳ፣የሚያውቅና የተጎዳ የለምና፡፡
- ለተከሳሽ ዋስትና ሲፈቀድ ለተጠቂው ስጋት እንዳይሆን ከውሳኔ በፊት ማሳተፍ ይቻላል/ይገባል ለምሳሌ አስገድዶ መድፈር ወ/ል የተፈጸመባቸው ህጻናት ሲሆኑ
- ዐ/ህግ ከምርመራ በሁዋላ መዝገቡን በመዝጋትና አያስከስስም ውሳኔ ሲሰጥ ተጠቂው እንዲያውቀው በማድረግ ቀጣይ አቤቱታውን ለሚመለከተው አካል ማቅረብ እንዲችል ዕድል መስተጥ ያስፈልጋል
- በግል አቤቱታ የሚቀርቡ ክሶች ላይም ከጠቂው ውጭ ጣልቃ ገብቶ ተጽዕኖ እንዳያደርግ መከላከል ያስፈልጋል፡፡
- አቅም ለሌላቸው ለወንጀል ተጎጅዎች በፍ/ብር ክስ መስርቶ ካሳ ማስከፈል ላይ ዐ/ህግ ስልጣን ተሰጥቶታል፣ይህን ስልጣኑን በተግባር ማሳየት ይገባል(6/ሸ፡ ክልል ጠ/ዐ/ህግ)፤ ወ/ል/ህ/ቁ 102(1) ለደረሰው ወንጀል ካሳ ማስከፈል

# የወንጀል ይግባኝ ሥ/ሥርዓት

1. ይግባኝ ማለት አንድ ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ የቀረበለትን የወንጀል ክስ በማቋረጥ ተከሳሹን ለጊዜው በመልቀቅ በሰጠው ትዕዛዝ፤ ወይም የቀረበለትን የወንጀል ክርክር ከህጉና ከማስረጃ ጋር አገናዝቦ በሚሰጠው የመጨረሻ ፍርድ ላይ ቅሬታ ያለው ሰው ቅሬታውን ለበላዩ ፍርድ ቤት አቅርቦ የተሰጠውን ትዕዛዝ/ፍርድ ትክክለኛነት የሚያስመረምርበት ሂደት ነው ማለት ይቻላል።
2. ዓላማው/የይግባኝ ሥርዓት ለመዘርጋት ያስፈለገበት፡- 1/ ሥህተቶችን ማረም 2/ ቁጥጥ ማድረግ ናቸው
3. የይግባኝ መብትና ወሰኑ፡ ይግባኝ ማለት ህገ መንግስታዊ መብት ነው(20/6) ነገር ግን መብቱ ፍጹም ሳይሆን በገደብ/በሁኔታ ላይ የተመሰረተ ነው(ሁሉ ነገር ይግባኝ ሊባልበት አይቻልም)። ለምሳሌ ሥ/ሥ/ህ 184 ጊዜያዊነት ያላቸው ትዕዛዞች ላይ ይግባኝ አይባልበትም ተብሎ ተገልጹወል።
4. የይግባኝ መብት በፌደራልና በክልል ፍ/ቤቶች፡- ሥ/ሥ/ህ 182-183 አሁን ተግባራዊ ስለማይሆን በፌደራል ሥርዓቱ መሰረት ክልልም ሆነ ፌደራል መንግስት ከወረዳ/መ.ደ.ፍ/ቤት/እስከ ሰበር ሰሚ ድረስ መዋቅር ስላለው ይግባኝ  የሚባለውም ለነዚሁ ደረጃ ላሉት ነው። 25/88 አንድ ይግባኝ ብቻ ነው ያለው ከዚያ ካለፈ ግን መ/ህ/ስተት ካለው ለማሳረም ሰበር ይቀርባል ይላል(9ና 13)
5. ቅጣት ላይ ካልሆነ ታምኖ ውሳኔ በተሰጠ ጉዳይ ጥፋተኝነት ላይ ይግባኝ የለውም
6. ከ185 አንጻር ይከላከል በተባለው ትዕዛዝ ላይ ይግባኝ ይባልበታል ወይ

7. ተከሳሽ በሌለበት የተሰጠ ፍርድ ና ይግባኝ ፡ ተከሳሽ በሌለበት ነገሩ ታይቶ ሲፈረድ ተከሳሹ ይህን ፍርድ ቀሪ እንዲደረግለት የሚጠይቅበት ሥነሥርዓት አለ። ይህም ተከሳሹ ነገሩ እርሱ ባለበት የመከላከያ ማስረጃዉን አቅርቦ የቀረበበትን ማስረጃ አግኝቶ መስቀለኛ ጥያቄ አቅርቦ እንዲፈረድ ከፈለገ ነዉ። በዚህ መሰረት የሚያቀርበዉ ጥያቄ በፍርድቤት ታይቶ ዉድቅ የማድረግ ዉሳኔ ከተሰጠ በዚህ ዉሳኔ ላይ ይግባኝ ማለት አይቻልም /የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ/ 202/3//።
8. በቅጣት ውሳኔ ላይ ይግባኝ ስለማለት (185)
9. የይግባኝ ጊዜ ና ጊዜው ስላለፈ ይግባኝ(187+191) 15 ቀን ይግባኝ ግልባጭ መጠየቂያ እና 30 ቀን ከ15 ውጭ ለቀጣይ ፍ/ቤ ይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ነው(187)። ይግበኝ ባይ በራሱ ጥፋት ባልሆነ ወይም ካቅሙ በላይ እንዲሁም በበቂ ምክንያት ጊዜው ማለፋን ማስረዳት አለበት።(191)
10. የይግባኝ ክርክር ሂደትና የይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት ዉሳኔ ፡ **192፣193፣194፣195፡ ሊያጸና፣ሊያሻሽል፣ሊሽር፣ወደ ታች ሊመልስ ፣ተጨማሪ ማስረጃ መስማት ይችላል።**

## ተከሳሽ በሌለበት የተሰጠን ፍርድ ቀሪ የማስደረግ

- ተከሳሽ በሌለበት የተሰጠን ፍርድ ቀሪ የማስደረግ ማመልከቻ አቀራረብና አወሳሰን(164፣197፣198
- ተከሳሽ በሌለበት የተሰጠን ፍርድ ቀሪ ለማድረግ ተቀባይነት ያላቸዉ ምክንያቶች
- ተከሳሽ በሌለበት የተሰጠ ፍርድ ቀሪ እንዲሆን በሚቀርብ ጥያቄ ላይ የሚሰጠዉ ዉሳኔ የሚያስከትለዉ ዉጤት (202)

# ስለቅጣት አፈጻጸም

- ቅጣት ከመፈጸሙ በፊት ስለሚገደብበትና ስለሚታገድበት ሁኔታ
- አወሳሰናቸው የሚገደቡ ቅጣቶች (191)
- አፈጻጸማቸው የሚገደቡ ቅጣቶች (192፣194፣196፣197
- አፈጻጸማቸው ለሌላ ጊዜ የሚተላለፍ (የሚታገድ /ቅጣቶች 202(2)፣200፣206፣204